# መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅ ላይ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ማሕበረሰብ የቀረበ አስተያየት

CCRDA

ሰኔ 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መግቢያ ..... 4
የረቂቅ ሕጉ እና የዚህ ጽሑፍ አቀራረብ ..... 5

የመጀመሪያ ክፍል
መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅን በሚመለከት ..... 7

I. የአዋጁ መግቢያ ..... 7

II ምዕራፍ አንድ ፤ የጋራ ድንጋጌዎች በሚመለከት (አንቀጽ 1 - 40) ..... 8

1. ክፍል አንድ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 1 - 3) ..... 8

1.1 የአዋጁ ስያሜ ..... 8
1.2 የመያድ ትርጓሜ ..... 8
1.2.1 ለመያድ የተፈቀዱ ዓላማዎች /ተግባሮች (Permitted purposes of NGOs) ..... 8
1.2.2 በመያድነት ሊቋቋሙ ስለሚችሉ የድርጅት ዓይነቶች (Types of legal entities / organizations that can be constituted as NGOs) ..... 9
1.2.3 ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ስለመንቀሳቀስ ..... 10
1.2.4 በተጠቃሚዎች መካከል በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከት በመሳሰሉት ልዩነት ስለማድረግ ..... 10
1.3 የተፈጻሚነት ወሰን ..... 11

2. ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች፤ የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤትና ስለ ምዝገባ (አንቀጽ 4-22) ..... 11

2.1 ስለ መያድ ምዝገባ ጽ/ቤት ..... 12
2.1.1 የምዝገባው ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር ..... 12
2.1.1 የአማካሪ ኮሚቴ ..... 12
2.2 ስለ ምዝገባ ..... 13
2.2.1 የምዝገባ ማመልከቻ ይዘት ..... 13
2.2.2 የምዝገባ ማመልከቻ አባሪዎች ..... 15
2.2.3 የምዝገባ ማመልከቻና አባሪዎቹን ስለማጣራት ..... 16
2.2.4 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ወይም ስለመከልከል ..... 17
2.2.5 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለሚያገለግልበት ዘመን (Validity period of the registration certificate) ..... 19
2.2.6 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ ..... 22

3. ክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ፤ ስለ መብቶችና ግዴታዎች (አንቀጽ 23 - 26) ..... 23

3.1 ስለ መርሕ ..... 23
3.2 ስለ ስም ..... 23
3.3 ስለ ሕጋዊ ሰውነትና ችሎታ ..... 23
3.4 ስለ ሌሎች ግዴታዎች እና ክልከላዎች ..... 24

CCRDA

4. ክፍል አራት ፤ ስለ ሪፖርትና ቁጥጥር (አንቀጽ 27- 30) ..... 26

4.1 ስለ መሠረዝ ..... 26
4.2 ስለ አዲትና ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ..... 26
4.3 ስለ ልዩ ምርመራ ..... 26

5. ክፍል አምስት፤ ስለ መያድ መፍረስ፣ መሠረዝ እና ሒሳብ ማጣራት (አንቀጽ 31- 40)..... 27

5.1 መያድ ስለሚፈርስባቸው ሁኔታዎች ..... 27
5.2 በፈቃደኝነት ስለ መፍረስ ሁኔታ ..... 29
5.3 ስለ ሒሳብ ማጣራት ..... 29
5.4 ስለ መያድ መለዋወጥ እና መቀላቀል ..... 29
5.4.1 ስለ መያድ መዋሃድ ..... 29
5.4.2 ስለመያድ መለያየት ..... 31
5.4.3 የውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ መለወጥ ..... 31

III ምዕራፍ ሁለት ፤ ስለ ማህበራት (አንቀጽ 41- 65) ..... 32

1. ሁለት የማህበር ዓይነቶችን በተመለከተ ..... 32
2. የቦርድ ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ ..... 33
3. ስለ ድርጅታዊ አወቃቀር ..... 34

IV ምዕራፍ ሶስት ፤ ስለ በጎ አድራጐት ድርጅት (አንቀጽ 66 - 88) ..... 34

V ምዕራፍ አራት ፤ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 89 - 99) ..... 35

1. ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ..... 35
2. ስለ ታክስ እና ቀረጥ ነጻ መብት ..... 35
3. ስለ መያድ ሕብረት (Umbrella Organizations) ..... 36
4. ስለ ይግባኝ ..... 36
5. ስለ መሸጋገሪያ ድንጋጌ ..... 38

ሁለተኛ ክፍል
የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት መቋቋምን በሚመለከት ..... 39

CGRDA

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) ማሕበረሰብ ይህን ዘርፍ የሚመለከት እራሱን የቻለና የተሟላ ሕግ እንዲወጣ ሲጠይቅ ቆይቷል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፍትሕ ሚኒስቴር "መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር" ረቂቅ አዋጅን አዘጋጅቶ ለውይይት ማቅረቡን የመያድ ማሕበረሰብ በአድናቆት ተቀብሏል::

በዚህ ረቂቅ አዋጅ ላይ ለመወያየት እና ሐሳብ ለማሰባሰብ የፍትሕ ሚኒስቴር ከ CRDA፣ Pact – Ethiopia፣ Action Aid እና British Embassy ጋር በመተባበር ከግንቦት 26 – 27, 1994 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በአካሄደው አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት በርካታ የአገር ውስጥና የውጭ አገር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የልዩ ልዩ የፌዴራልና የክልል መንግሥት መ/ቤቶች ተወካዮች፣ የተለያዩ ባለሙያ ግለሰቦች እና እንዲሁም የሰፊ ሲቪል ማህበረሰብ አባሎች ተሳትፈዋል::

በዓውደ ጥናቱ ላይ የፍትሕ ሚኒስቴር ባለሙያዎች እና የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያና መግለጫ ሰጥተዋል:: እንዲሁም በዚሁ ዓውደ ጥናት ላይ የመያድ ማህበረሰብ የሕግ ጉዳይ ምክክር ግብረ ኃይል (NGO Legal Framework Consultative Task Force) በረቂቅ ሕጉ ላይ ያለውን የቅድሚያ አስተያየት (Preliminary Observations) አቅርቧል::

ዓውደ ጥናቱ በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት እና በጥልቀት የተወያየ ሲሆን ከየቡድኖቹ በቀረቡት ሪፖርት መሠረት የመያድ ማሕበረሰብ የሕግ ጉዳይ ምክክር ግብረ ኃይል ያቀረበውን አስተያየት ከመደገፍ በተጨማሪ ረቂቅ አዋጁ ሊሻሻልና ሊስተካከል ስለሚገባበት ጉዳዮች በርካታ ጠቃሚ አስተያየቶች ቀርበዋል::

በዚህ አገር ዓቀፍ ዓውደ ጥናት የተሳተፉት የመያድ ማሕበረሰብ ተወካዮች በዓውደ ጥናቱ የተነሱት አስተያየቶች በአግባቡ ተሰባስበውና ተጠናቅረው ለሕግ አርቃቂው ኮሚቴ እና ለሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ እንዲቀርብ በወሰኑት መሠረት ይህ የመያድ ማሕበረሰብ አስተያየት ተዘጋጅቷል::

የዓውደ ጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት የመያድ ማሕበረሰብ ተወካዮች በአሳለፉት ውሳኔ መሠረት የመያድ ማሕበረሰብ የሕግ ጉዳዮች የምክክር ግብረ ኃይል ይህን ኃላፊነት ወስዶ የመያድን ማህበረሰብ አቋም የሚያንፀባርቅ አስተያየት እንዲያቀርብ በተጠየቀው መሠረት ግብረ ኃይሉ በጉዳዩ ላይ ሰፊ እና ጥልቅ ውይይት በማድረግና በዓውደ ጥናቱ ላይ የተነሱትን ጠቃሚ ሐሳብና አስተያየቶች ሁሉ በማሰባሰብ ይህን የመያዱን ማሕበረሰብ አስተያየት በዚህ ጽሑፍ አማካኝነት ያቀርባል::

የፌዴራሉ መንግሥት የፍትሕ ሚኒስቴር የመያድ ምዝገባና አሠራር በተመለከተ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለውይይት በማቅረቡ የመያዱ ማሕበረሰብ አድናቆቱን እየገለጸ የሚኒስቴሩ መ/ቤት እና የሕግ አርቃቂው ኮሚቴ ከመያዱ ማሕበረሰብ የቀረበውን አስተያየት በቂ ትኩረት እንደሚሰጠውና ረቂቅ ሕጉ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል እንደሚያደርግ ያለውን እምነት እና ተስፋ ከወዲሁ ለመግለጽ ይወዳል::

CRDA

የፌዴራሉ ፍትሕ ሚኒስቴር የረቂቅ ሕጉን መወያያ ዓውደ ጥናት ከመያዱ ማሕበረሰብ ጋር በመተባበር በማዘጋጀት፣ ዓውደ ጥናቱ በክቡር ምክትል ሚኒስትሩ ሰብባቢነት እንዲመራ በማድረግ እና የመያዱ ማሕበረሰብ አስተያየቱን በነፃነት ስሜት እንዲያቀርብ በማድረግ ያሳየው ቁርጠኝነት እና የበጎ ፈቃድ ስሜት አሁንም በዚህ ጽሑፍ የቀረቡ የመያዱ ማሕበረሰብ አስተያየቶች በቂ ትኩረት እንደሚያገኙና በዚሁ መሠረትም ተገቢው ማሻሻያዎች እንደሚደረጉ የመያዱን ማሕበረሰብ እምነት እና ተስፋ የላቀ ያደርገዋል::

## የረቂቅ ሕጉ እና የዚህ ጽሑፍ አቀራረብ

ረቂቅ ሕጉ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን እነዚህም:-

- ምዕራፍ አንድ ፤ የጋራ ድንጋጌዎች
    - ስለ መዝጋቢው ጽ/ቤት
    - ስለ ምዝገባ
    - ስለ መብትና ግዴታዎች
    - ስለ ሪፖርትና ቁጥጥር እና
    - ስለ መፍረስ፣ ሂሳብ ማጣራትና መሠረዝ
- ምዕራፍ ሁለት ፤ ስለ ማሕበራት
    - ማህበር ስለማቋቋም
    - ስለ ማህበር አባሎች
    - ስለ አስተዳደር
- ምዕራፍ ሶስት ፤ ስለ በጎ አድራጎት ድርጅት
    - ስለ መቋቋም እና ምዝገባ
    - ስለ አስተዳደር
- ምዕራፍ አራት ፤ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
    - ስለ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ
    - ስለ ታክስና ቀረጥ መብቶች
    - ስለ መያድ ሕብረት ማቋቋም እና
    - ስለ ይግባኝ የሚደነግጉ ናቸው::

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማሳየት የተፈለገው የረቂቅ አዋጁን አቀራረብ ሲሆን የዚህ ጽሑፍ አቀራረብ ደግሞ በሁለት ዋነኛ ክፍሎች የተከፈለ ነው::

CGRDA

የመጀመሪያው ክፍል በረቂቅ አዋጁ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ አስተያየት እና የማሻሻያ ሐሳቦች የሚቀርቡበት ሲሆን ለቀላል አነባበብ እና ንዕዕር እንዲረዳ አቀራረቡ በተቻለ መጠን የረቂቅ አዋጁን አቀራረብ እና ቅደም ተከተል መሠረት አድርጐ የሚቀርብ ነው::

ሁለተኛው ክፍል የመያድ ማሕበረሰብ የመያድ የሥራ እንቅስቃሴ ጉዳዮችን (Operational activities) በሚመለከት አንድ እራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ አካል እንዲቋቋም ሲያቀርቡት የነበረውን ጥያቄ የሚመለከት ነው::

ረቂቅ አዋጁን በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያው ክፍል ላይ የቀረቡት አስተያየት እና የማሻሻያ ሐሳቦች ከዚህ በፊት በሥራ ላይ በነበሩ እና አሁንም ያሉ አግባብነት ያላቸውን ሕጐች መሠረት በማድረግ፣ የመያድን ነባራዊ ሁኔታ በማጤን፣ የሌሎች አገሮችን ልምድ በማገናዘብ፣ እና መንግሥት የጠቅላላውን ጥቅም ለማስጠበቅ ያለበትን ኃላፊነት በመገንዘብ የተሰጡ አስተያየቶች መሆናቸውን ለመግለጽ እንወዳለን::

CCRDA

# የመጀመሪያ ክፍል

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅን በሚመለከት

### I. የአዋጁ መግቢያ

የአዋጁ መግቢያ መያድ በአገሪቷ የማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥረት ውስጥ ያለውን ሚና፣ ጠቀሜታ እና አስተዋጽኦ በተገቢው መንገድ የሚገልጽ ሊሆን ይገባዋል::

የአንድ ሕግ መግቢያ ክፍል ሕጉ ያስፈለገበትን ማህበራዊ፣ ወይም ፖለቲካዊ፣ ወይም ኢኮኖሚያዊ፣ ወይም ሕጋዊ ምክንያቶች እና እሳቤዎች በተገቢው መጠን በመዘርዘር የሚያስረዳና የአዋጁን መንፈስ እና ዓላማ በግልጽ የሚያመለክት መሆን አለበት::

ስለሆነም የአዋጁ መግቢያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ነጥቦችን በሚያካትት እና በሚያንፀባርቅ መልኩ ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

- ~~መያድ ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የልማት እድገት አጋር (Partner) መሆኑን፣~~

- መያድ በተለይም ዝቅተኛውና በልዩ ልዩ ዕድሎች ተጠቃሚ ያልሆነውን የሕብረተሰብ ክፍል በመድረስ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን፣

- መያድ በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥረት ውስጥ እየተጫወተ ያለው እና ለወደፊትም ሊጫወት የሚችለው ሚና ሊበረታታ፣ ሊታገዝ እና አስፈላጊ ሁኔታዎች ሊመቻቹለት የሚገባ መሆኑን፣

- ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች እና ግለሰቦች በበጎ ፈቃደኝነት (Voluntarism) ስሜት በመነሳሳት በተደራጀ መልኩ የሚያደርጉት የሰብዓዊ ተግባርና የልማት ዕድገት ጥረት ሊበረታታ፣ ሊታገዝ እና ምቹ ሁኔታዎች ሊፈጠርለት የሚገባ መሆኑን፣

- በዓለም ዓቀፋዊ ስምምነቶች እና በአገሪቷ ሕጐችም የተጠበቁ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች መሠረት ሐሳብን በነፃ የመግለጽ እና በነፃነት የመደራጀት መብት በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን፣

- ስለዚህም የአዋጁ አላማ መሠረታዊ ከሆነ ሕገመንግሥታዊ ጥበቃ ከተደረገለት ሀሳብን በነፃ የመግለጽ እና የመደራጀት መብት በመነሳት በልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች እና ግለሰቦች የሚመሰረቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተሻሻለና በቀለጠፈ አሠራር የሚመዘገቡበትን እና ወደ ሥራ የሚሠማሩበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት ሁሉን ዓቀፍ በሆነው የአገሪቷ የእድገት ጥረት ውስጥ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ለማድረግ ማስቻል መሆኑን ሊገልጽ ይገባዋል::

CCRDA

## II ምዕራፍ አንድ ፤ የጋራ ድንጋጌዎች በሚመለከት (አንቀጽ 1 - 40)

### 1. ክፍል አንድ ድንጋጌዎች

#### 1.1 የአዋጁ ስያሜ

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የአዋጁ ስያሜ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር አዋጅ" የሚል ነው::
በእርግጥ አዋጁ ስለ መያድ ምዝገባ ሰፋ ያለ ክፍል ቢኖረውም ከምዝገባ ጉዳይ ውጪ እንደ መያድ መብትና ግዴታዎች፣ ስለ መያድ አመሠራረት እና አስተዳደር፣ ስለ መያድ ኃላፊነትና ተግባር፣ እንዲሁም ስለሌሎች የመያድ ልዩ መብቶችና ጉዳዮች ሁሉ የሚዘረዝር ሕግ በመሆኑ "የመያድ አዋጅ" (NGO Proclamation) በሚል ስያሜ መጠራቱ ተገቢ ስለሆነ አንቀጽ አንድ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል ሐሳቡ እናቀርባለን::

#### 1.2 የመያድ ትርጓሜ

##### 1.2.1 ለመያድ የተፈቀዱ ዓላማዎች /ተግባሮች (Permitted purposes of NGOs)

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(1)(ሠ) መሠረት የመያድ የተፈቀዱ ዓላማዎች /ተግባሮች ሆነው የተቀመጡት " . . . ለራሱ ሳይሆን ለሕብረተሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውን የማህበራዊ አገልግሎት፣ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ግንባታ፣ እንደአስፈላጊነቱ የእርዳታ ተግባራትን ለማከናወን. . ." የሚል ነው::

በእርግጥ በረቂቅ አዋጁ የተዘረዘሩት እነዚህ ዓላማዎች/ተግባሮች መያድ በብዛት የሚቋቋምባቸው ዓላማና ተግባር መሆናቸው ቢታወቅም በአጠቃላይ መያድ የሚቋቋመው ግን በዚህ ዝርዝር ላይ ለተመለከቱት የተወሰኑ ዓላማና ተግባር ብቻ አይደለም::

በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተመለከቱት ዓላማና ተግባሮች በተጨማሪ መያዶች በልዩ ልዩ ሌሎች ሕጋዊ ዓላማና ተግባር ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ፣ ወደፊትም ሊሠማሩ ይችላሉ::

ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል እንደ ጥናትና ምርምር፣ ትምህርት፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የተሟጋችነት (Advocacy) ሥራ፣ የፖሊሲ ጥናትና ውይይት፣ የሰብዓዊ መብቶች ማስፋፋትና ጥበቃ፣ የልዩ ልዩ ሕብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅም ጥበቃ፣ የእንስሳት ደህንነት ጥበቃ፣ . . . ወዘተ ለመጥቀስ ይቻላል::

ከዚህ በላይ ለአብነት ያህል ለመዘርዘር የተሞከረው መያድ የተሠማራበትና ሊሠማራበት የሚችለው ዓላማና ተግባር የቱን ያህል ሰፋ ያለ መሆኑን ለማሳየት ነው::

CCRDA

ስለሆነም ድንጋጌው መያድ የተሠማራበትን እና ወደፊትም ሊሠማራ የሚችልበትን ሕጋዊ ዓላማዎች ሁሉ በማይገድብና ሰፋ ባለ ሁኔታ በመተርጐም ሰፋ ያሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ሕጋዊ ዓላማዎችን ለማራመድ በሚያስችል መልኩ ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስተያየት እናቀርባለን:: የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ አሁን በቀረበበት መልኩ የመያድን ዓላማና ተግባር በተወሰኑ ዓላማዎች ዝርዝር (exclusive list of purposes) የሚያስቀምጥ በመሆኑ ከላይ በተገለጸው መሠረት እንዲሻሻል እንጠይቃለን::

### 1.2.2 በመያድነት ሊቋቋሙ ስለሚችሉ የድርጅት ዓይነቶች (Types of legal entities / organizations that can be constituted as NGOs)

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(2) እና (3) ድንጋጌዎች መሠረት በአገር ውስጥ የሚመሠረት መያድ ሊቋቋም የሚችለው በአዋጁ ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች መሠረት በ "ማሕበር" መልክ ወይም በአዋጁ ምዕራፍ ሶስት ድንጋጌዎች መሠረት በ "የበጎ አድራጐት ድርጅት" መልክ ብቻ ነው::

በ1952 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ዓላማቸው ለትርፍ ያልሆነና መንግሥታዊ ያልሆኑ ሶስት ዓይነት ተቋሞችን ለመመስረት እንደሚቻል ይደነግጋል:: እነዚህም:-

- ማሕበር (Association)
- የበጎ አድራጐት ድርጅት (Endowment) እና
- ለልዩ በጎ አድራጐት የሚውል የአደራ ንብረት (Trust) ናቸው::

ከእነዚህ ሶስት ዓይነት ተቋሞች ውስጥ ረቂቅ ሕጉ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ዓይነት ተቋሞች ብቻ በመምረጥ ሶስተኛውን ዓይነት ተቋም ሳያካትተው ቀርቷል::

ይህ ሶስተኛው ዓይነት በእንግሊዘኛ ቋንቋ Trust የሚባለው ተቋም እንደ የበጎ አድራጎት ድርጅት (Endowment) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የግል ሀብታቸውን ወይም ከሀብታቸው የተወሰነ ክፍልን ትርፍ ማግኘት ላልሆነ ለጠቅላላ ጥቅም ዓላማ የሚያውሉበት መንገድ ነው::

ይህ Trust የሚባለው ተቋም ወይም ድርጅት በብዙ አገሮች በስፋት የሚታወቅና በተለይም አነስተኛ ለሆነና በአንድ የተወሰነ ዓላማ ላይ ብቻ ለሚያተኩር ተግባር ዓይነተኛ ተስማሚነት ያለው በመሆኑ የዚህ ዓይነት ተቋም በሕግ ዕውቅና ሊሰጠውና ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ነው::

በእርግጥ በአገራችን እስከ አሁን ድረስ በዚህ መልክ የተመሰረቱ ድርጅቶች ስለመኖራቸው በብዛት ባይታወቅም ለወደፊቱ ግለሰቦች የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራቸውን በተደራጀና የሕግ ጥበቃ በሚደረግለት መልኩ ለማስፈጸም የሚያስችላቸው ተቋም በመሆኑ በዚህ ረገድም ሊበረታታ የሚገባው እና በሕግ ሊፈቀድ የሚገባው ተቋም ነው::

CCRDA

ስለሆነም አዋጁ ከ "ማሕበራት" እና "የበጎ አድራጐት ድርጅት" በተጨማሪ በፍትሐብሔር ሕጉ እስከ ዛሬ ድረስ እውቅና ተሰጥቶት ያለውን "Trust" የተሰኘውን ተቋም እውቅና እንዲሰጠውና መያድ ሊቋቋም ከሚችልባቸው ሕጋዊ ተቋሞች ውስጥ እንደ አንዱ ሆኖ በሕጉ ውስጥ እንዲካተት አስተያየት እናቀርባለን::

### 1.2.3 ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ስለመንቀሳቀስ

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(1)(መ) ድንጋጌ መሠረት ለመያድ ከተሰጡት የትርጓሜ ነጥቦች ውስጥ አንዱ "...ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚንቀሳቀስ . . ." የሚል ነው::
ለአንድ መያድ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ክልል የሚንቀሳቀስ መሆኑ ለመያድ ምንነት መገለጫ ባህሪይ (Defining feature) አይሆንም::

የአንድ መያድ መገለጫ ባህሪያት በአንቀጽ 2(1) ሥር የተመለከቱት እንደ ዋነኛ ዓላማው፣ ለትርፍ ያልተመሠረተ መሆኑ፣ መንግሥታዊ አለመሆኑ፣. . . ወዘተ የመሳሰሉት እንጂ የሥራ እንቅስቃሴው በአንድ ወይም ከአንድ ክልል በላይ መሆን እና አለመሆኑ አይደለም::

ምናልባትም ይህ ንዑስ አንቀጽ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሊመዘገቡ ስለሚችሉ መያድ ዓይነቶች ለመግለጽ ታስቦ ከሆነ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጐበት ምዝገባን ወደሚመለከተው የአዋጁ ክፍል ውስጥ ሊካተት የሚገባው ይሆናል::

የምዝገባ ጉዳይን በተመለከተም ቢሆን አንድ መያድ የሥራ እንቅስቃሴው በአንድ ክልል የተወሰነ መሆኑ ብቻ መያዱ በፌዴራል የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤት ከመመዝገብ ሊያግደው የሚችል ተደርጐ መወሰድ የሌለበት መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን::

ስለሆነም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(1) በፊደል ተራ (መ) ሥር የተመለተው ያለቦታው የተቀመጠ በመሆኑ እንዲታረም አስተያየት እናቀርባለን::

### 1.2.4 በተጠቃሚዎች መካከል በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከት በመሳሰሉት ልዩነት ስለማድረግ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(1)(ሐ) መያድ በተጠቃሚዎች መካከል በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከት በመሳሰሉት ልዩነት ሊያደርግ እንደማይገባ ይደነግጋል::

ይሁንና አንድ ዓይነት ብቻ የጸታ ቡድንን፣ በዘር ወይም በብሔር ተለይቶ የሚታወቅ አንድ ክልልን፣ በቋንቋ ተለይቶ የሚታወቅ አንድ የሕዝብ ክፍልን በተለይ ለማገልገል የተቋቋሙና ሊቋቋሙም የሚችሉ ድርጅቶች በመኖራቸው የዚህን ንዑስ አንቀጽ አግባብነት አከራካሪ ያደርገዋል::

CGRDA

ሕገ መንግሥታዊ የእኩልነት መብትን በተመለከተ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 ስር ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውንና በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ የሚደረግላቸውና በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጸታ፣ በመሳሰሉት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት እንዳላቸው ተደንግጓል::
በመሆኑም ምናልባት በመያድ ተግባር ለዚህ የእኩልነት መብት ተቃራኒ የሆነ ክስተት ቢገኝ ከሕገመንግሥታዊው ድንጋጌም አንጻር ሊታይ የሚችል ነው::

ስለሆነም በተቋቋሙበት ዓላማ መሠረት በዘር ወይም በብሔር ወይም በቋንቋ ወይም በጸታ ተለይቶ የሚታወቅ የሕብረተሰብ ክፍልን የሚያገለግሉ ድርጅቶች ስላሉና ፤ አጠቃላይ የሆነውን የሰው ልጆች እኩልነት መብት በሚመለከትም ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ያለው በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2(1) (ሐ) ሥር የተመለተው አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲታረም አስተያየት እናቀርባለን::

1.3 **የተፈጻሚነት ወሰን**

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 3 የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን ይደነግጋል:: በዚህ አንቀጽ ስር ከዚህ የሚከተሉት ሁለት ነጥቦችን በማስታወስ አስተያየት እናቀርባለን::

- የጸታ አገላለጽን በተመለከተ:- በአዋጁ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ የተለምዶ አገባብ በወንድ ጸታ የተደነገገው ሁሉ ለሁለቱም ጸታዎች በእኩልነት ተጠቃሽ መሆኑን የሚገልጽ አንድ ንዑስ አንቀጽ እንዲጨመር እና

- በአንቀጽ 3(1) የተመለከተው የመያድ የተፈቀዱ ዓላማዎች /ተግባሮች ስለዚሁ ጉዳይ በአንቀጽ 2(1) (ሠ) ላይ በተሠጠው አስተያየት መሠረት ተሻሽሎ እንዲጸፍ እናስታውሳለን::

2. **ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች፤ የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤትና ስለ ምዝገባ (አንቀጽ 4-22)**

የረቂቅ አዋጁ ምዕራፍ አንድ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች ስለ መዝጋቢው ጽ/ቤት እና ስለምዝገባ የሚደነግጉ ቢሆንም የክፍል ሁለት ርዕስ "ምዝገባ" ብቻ የሚል ነው:: በዚህ ክፍል ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች እራሳቸውን የቻሉ ሁለት ዋና ክፍሎች በመሆናቸው ከዚህ በታች እንደተመለከተው እንዲስተካከል አስተያየት እናቀርባለን::

- ከአንቀጽ 4 – 12 ያሉት ድንጋጌዎች የመዝጋቢውን ጽ/ቤት የሚመለከቱ ስለሆነ እነዚህ ድንጋጌዎች በክፍል ሁለት ውስጥ ሆነው የዚህ ክፍል ርዕስም "የምዝገባ ጽ/ቤት" በሚል እንዲስተካከል እና

- ከአንቀጽ 13 – 22 ያሉት ድንጋጌዎች ምዝገባን የሚመለከቱ ስለሆነ እነዚህ ድንጋጌዎች በክፍል ሶስት ስር ሆነው የክፍሉ ርዕስም "ምዝገባ" የሚል እንዲሆንና የቀጣዮቹ ክፍሎች ተራ ቁጥር በዚሁ መሠረት እንዲስተካከል አስተያየት እናቀርባለን::

CCRDA

ከዚህ በላይ የተገለጸው የአዋጁን አቀራረብ /አቀራረጽ (drafting) በሚመለከት የቀረበ ማስታወሻ ሲሆን የመዝጋቢው ጽ/ቤት እና ምዝገባን በተመለከቱ ጉዳዮች ያለንን አስተያየት ከዚህ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እናቀርባለን::

## 2.1 ስለ መያድ ምዝገባ ጽ/ቤት

### 2.1.1 የምዝገባው ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 6 የምዝገባ ጽ/ቤትን ሥልጣንና ተግባር ይዘረዝራል:: የጽ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ለሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች ለማስታወስ እንወዳለን::

- በአንቀጽ 6(1) ሥር ጽ/ቤቱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይመዘግባል የሚለው ንዑስ አንቀጽ ጽ/ቤቱ መያድን ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ 3(2) መሠረት ወደፊት ልዩ ሕግ እስኪወጣ ድረስ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሌሎች ዓይነቶችንም ድርጅቶች የሚመዘግብ መሆኑን በሚገልጽ መልኩ ተሻሽሎ ቢፃፍ፣

- በአንቀጽ 6(5) መሠረት ጽ/ቤቱ ምዝገባን ሊሰርዝ ስለመቻሉ የተደነገገው በዚህ ጽሑፍ ስለ ምዝገባ መሠረዝ ጉዳይ በምንሰጠው አስተያየት መሠረት ተስተካክሎ እንዲጻፍ እና

- ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የመያድን መለዋወጥ እና መቀላቀል (Conversion and Amalgamation) በተመለከተ ተቀብሎ እንደሚያፀድቅና እንደሚመዘግብ የሚገልጽ ንዑስ አንቀጽ እንዲጨመር ሐሳብ እናቀርባለን::

### 2.1.1 የአማካሪ ኮሚቴ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 11 እና 12 ምዝገባ ጽ/ቤቱ የአማካሪ ኮሚቴ እንደሚኖረውና የኮሚቴው ተግባርም ምን እንደሆነ ይደነግጋል::
ይህ የአማካሪ ኮሚቴ የሚቋቋመውም ከተለያዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶች በተውጣጡ ተወካዮች እንደሆነ ተደንግጓል::

የመያድ ማሕበረሰብ በዚህ የአማካሪ ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ለኮሚቴው ተግባሮች እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው::

ስለሆነም የዚህ አማካሪ ኮሚቴ 1/3 (አንድ ሶስተኛ) አባሎች ከተለያዩ ዓይነት መያዶች (ለምሳሌም የውጭ አገር መያዶች፣ የአገር ውስጥ መያዶች፣ . . .) የሚወከሉበትና ከዚህ በተጨማሪም ኮሚቴው ለተግባሩ የሚጠቅሙ ግለሰቦችን በአባልነት ሊያሳትፍ በሚችልበት መልኩ ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስተያየት እናቀርባለን::

CCRDA

ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 12(2) እና (3) ሥር ኮሚቴው የመፍትሔ ሐሳቦችን ለሚኒስትሩ ያቀርባል የሚለው "ለሚኒስትሩ ወይም ለምዝገባ ጽ/ቤቱ ያቀርባል" በሚል እንዲስተካከል አስተያየት እናቀርባለን::

የአማካሪ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያቀርባቸው አስተያየቶች ግን የግድ ለሚኒስትሩ ብቻ እንዲሆኑ የሚያስፈልግበት ምክንያት የለም:: ይልቁንም የምዝገባ ጽ/ቤቱ በሚቀርቡለት ሐሳቦች መሠረት እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችለው ስለሆነ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ አስተያየቶችን ለምዝገባ ጽ/ቤቱ ማቅረቡ ጠቃሚ ነው::

ስለ አማካሪ ኮሚቴው አቋቋምና አሠራር አዋጁ በዝርዝር ስለማይገልጽና ምናልባትም በዚህ አዋጅ የዚህ ዝርዝር ሁኔታ ሊገለጽ እንደማይችል የሚጠበቅ ስለሆነ የአማካሪው ኮሚቴ መቋቋምና ሥራ መጀመር፣ የአሠራሩ ሁኔታ እና አስፈላጊውን የሎጂስቲክ ድጋፍ በሚመለከት የምዝገባ ጽ/ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት የሚወሰን መሆኑ እንዲገለጽ አስተያየት እናቀርባለን::

## 2.2 ስለ ምዝገባ

### 2.2.1 የምዝገባ ማመልከቻ ይዘት

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15 የመያድ ምዝገባ ማመልከቻ ሊይዝ የሚገባውን መረጃዎች ይዘረዝራል:: ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ በንዑስ አንቀጽ (5)፣ (9) እና (11) የተመለከቱት ለመያድ ምዝገባ ጉዳይ አስፈላጊ ያልሆኑና አንድን መያድ ከመመዝገብ በፊት በሃሳባዊ መስፈርቶች የመመዘን ወይም የመገምገም ጠባይ ያላቸው በመሆኑ የሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መርሆና ነጥቦች መሠረት በማድረግ እንዲያርማቸው አስተያየታችንን እናቀርባለን::

- በመያድ ምዝገባ ሂደት ዋነኛና መሪ መርህ ሊሆን የሚገባው የመያድ በቀለጠፈ፣ ቢሮክራሲያዊ ባልሆነ፣ ቀላል እና ፈጣን በሆነ፣ የተወሰነ አግባብነት ያላቸውን መረጃና ሰነዶች በሚጠይቅ ሥርዓት የመመዝገብን አስፈላጊነት ነው::

- ለምዝገባው ሒደት አስፈላጊ የሚሆነው ዋነኛው ሰነድ በሕጉ መሠረት የተዘጋጀው የማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ሲሆን ይህም ስለመያዱ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘ ነው::

- በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከተመለከቱት መሠረታዊ መረጃዎች ውጪ ሊጠየቁ የሚችሉ ተጨማሪ መረጃዎች ቢኖሩ ለምዝገባው አገልግሎት አስፈላጊ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ሕጉ አስቀድሞ ሊደነግጋቸው ይገባል::

- ለምዝገባው አገልግሎት አስፈላጊ ያልሆኑና በተለይም መያዱን ከመመዝገቡ በፊት በተለያዩ መስፈርቶች ለመመዘን የሚፈልጉ መረጃዎች መሠረታዊ በሆነ የመደራጀት መብት ላይ ቅድመ ሁኔታዎችን መጫን ስለሚሆን ትክክል አይደለም::

CGRDA

- በዚህ ረገድ በአንቀጽ 15(5) ፣ (9) እና (11) ሥር በምዝገባ ማመልከቻ ላይ የተጠየቁት መረጃዎች በማናቸውም መልኩ ለምዝገባው አገልግሎት አስፈላጊ ያልሆኑና ለመመዝገብ የቀረበውን መያድ ለምዝገባ አገልግሎት አስፈላጊ ባልሆኑ መረጃዎች ለመመዘን ወይም ለመገምገም እና በዚህ ዓይነቱ ግምገማና መመዘኛም የምዝገባው ጽ/ቤት ከተግባሩ ውጪ ሰፊ የሆነ ቢሮክራሲያዊ ሥልጣን (bureaucratic discretion) የሚሰጠው ስለሆነ ለምዝገባ አሠራር እንቅፋት የሚፈጥር ነው::

- በአንቀጽ 15(5) እንዲሁም አንቀጽ 16(3) ሥር ". . . የመያዱ በሕርይ ለሌሎች የማስፈጸሚያ ገንዘብ ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚሰጥ ወይም በራሱ የሚያስፈጽም ስለመሆኑ . . ." በሚል የተጠየቀው መረጃ የመያድን ባህርይ የአንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ገንዘብ ሰጪ ወይም ገንዘብ ተቀብሎ አስፈጻሚ አድርጐ በጠባቡ ከማየት የመነጨና፤ የበጎ ፈቃደኝነትን (Voluntarism) አስተሳሰብ የዘነጋ፣ የመያድ ማቋቋም ከመሠረታዊ የመደራጀት መብት የሚመነጭ መሆኑን የማያስተውል በመሆኑም ጭምር ከመረጃው አላስፈላጊነት በተጨማሪም ፅንሠ ሐሳቡ በሕግ ሊደነገግ የማይገባው ነው::

- በአንቀጽ 15(9) ". . . መያዱ በከፍተኛ የአመራር ደረጃ ሊቀጥራቸው ያሰባቸው ሠራተኞች ብዛት፣ ዜግነት፣ የትምህርት ደረጃና ዓይነት እንዲሁም የደመወዛቸው መጠን. . ." የሚለው እና እንዲሁም በአንቀጽ 15(11) "... መያዱ ሊንቀሳቀስባቸው ከመረጣቸው አካባቢዎች ውጪ በሌሎች አካባቢዎች እንዲሠራ ቢደረግ ያለው ፈቃደኝነት..." የሚሉት ለምዝገባ አገልግሎት የማያስፈልጉ መረጃዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ በውስጣቸው ያዘሉትም ፅንሠ ሐሳብ ሕገ መንግሥታዊ ከሆነ የመደራጀት እና ሕጋዊ ዓላማዎችን ይዞ ከማራመድ መብት ጋር የማይጣጣም ነው::

- በሌላ በኩል የተጠቀሱት መረጃዎች ገና መያዱ ለምዝገባ በቀረበበት ወቅት ተሟልተውና ተጠናቅረው ሊታወቁም የሚችሉ አይደሉም፣ ከፊሎቹም በሒደት ሊለዋወጡ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው::

- በአጠቃላይ ለመያድ ምዝገባ ሊጠየቁ የሚገባቸው መረጃዎች ለመያዱ ምዝገባ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ ስለሆነ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ንዑስ አንቀጾች እንዲታረሙ አስተያየት እናቀርባለን::

- በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15(4) "... መያድን እንዲመሩ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው መሥራች አባላት..." የሚለው "የመያዱ መሥራች አባላት" በሚል ሊስተካከል የሚገባው መሆኑን እናስታውሳለን::
በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ 15(4) የተጠየቀው መረጃ አግባብነቱ በአገር ውስጥ አዲስ ለሚቋቋም መያድ እንጂ በውጭ አገር ለተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ለመመዝገብ ጥያቄ ለሚያቀርብ መያድ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ንዑስ አንቀጹ ይህንኑ በሚገልጽ መልኩ ተሻሽሎ ሊፃፍ እንደሚገባ ለማስታወስ እንወዳለን::

CCRDA

### 2.2.2 የምዝገባ ማመልከቻ አባሪዎች

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 16 ከምዝገባ ማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸውን ሰነዶች ይዘረዝራል::

በቅድሚያ በሕግ ማርቀቅ (Drafting) ቴክኒክ አንጻር አንቀጽ 15 እና 16 በአንድነት ሆነው አጠር ባለ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ሊጻፍ መቻሉን እያስታወስን በአንቀጽ 16 ስር ስለተጠቀሱት አባሪ መረጃዎች ጉዳይ የሚከተለውን አስተያየት እናቀርባለን::

- በአንቀጽ 16(1) (ሀ) ድንጋጌ መሠረት መያዱ የበጎ አድራጐት ድርጅት ከሆነ የመመስረቻ ጽሑፉ ለውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገቡን የሚያመለክት ሕጋዊ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ተገልጿል::

- የበጎ አድራጐት ድርጅት የመመስረቻ ጽሑፍ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት እንዲመዘገብና እንዲረጋገጥ በሚል የተጠየቀው ቅድመ ሁኔታ ከዚህ በላይ ስለ መያድ ምዝገባ መርሕ በተራ ቁጥር 2.2.1 ስር ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንጻር ሊጤን የሚገባው ነው::

- የበጎ አድራጐት ድርጅት የመመስረቻ ጽሑፍ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ መጠየቁ የመያድን ምሥረታ እጅግ የተወሳሰበ፣ ውጣ ውረድ የበዛው እና ግለሰቦች የበጎ አድራጐት ድርጅትን እንዲያቋቁሙ ያማያበረታታ ይሆናል::

- የበጎ አድራጐት ድርጅት የሚመሠረትበት ዋነኛ ሰነድ ስጦታ ወይም ኑዛዜ የሚደረግበት ሰነድ ነው:: ይህም የስጦታ ወይም የኑዛዜ ሰነድ በወይነቱና በሥረ ነገሩ (its form and substance) በስጦታና በኑዛዜ ደንቦች የሚመራ ነው:: በእነዚህ ደንቦች መሠረት በሕግ ፊት የሚጸና ስጦታ ወይም ኑዛዜ ለማድረግ የሰነዱን በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገብ የግድ አይልም:: በእርግጥ የስጦታው ወይም የኑዛዜ ሰነዱ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሊመዘገብ ቢችልም፤ አለመመዝገቡ ግን በሕግ ፊት ዋጋ ያሳጣዋል ማለት አይደለም::

- ስለሆነም የበጎ አድራጐት ድርጅቱ የተመሠረተበት ሰነድ በወይነቱና በሥረ ነገሩ (its form and substance) በስጦታና የኑዛዜ ደንቦች መሠረት የተሟላ ሆኖ እስከቀረበ ድረስ የግድ በውል ክፍል መመዝገብ የማያስፈልገው በመሆኑ አንቀጽ 16(1)(ሀ) እንዲታረም አስተያየት እናቀርባለን::

CCRDA

### 2.2.3 የምዝገባ ማመልከቻና አባሪዎቹን ስለማጣራት

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 17 የምዝገባ ጽ/ቤቱ ለምዝገባ የቀረበለትን ማመልከቻና አባሪዎች ለማጣራት የሚወስደውን እርምጃዎች ይገልጻል::
በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና(3) ላይ ያለንን አስተያየት ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን::

- በአንቀጽ 17(2) ሥር የመያዱ ዓላማ "... ለሥነ ልቡና..." ተቀራኒ አለመሆኑ የሚለው ግልጽ ያልሆነና ምናልባት በሃሳባዊ ትርጉም ሕገ መንግሥታዊ ለሆነ የመደራጀት መብት እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል እንዲታረም አስተያየት እናቀርባለን::

- በአንቀጽ 17(3) ሥር መዝጋቢው ጽ/ቤት "... የመያዱ መሥራች አባላት በሙስና ያልተበከሉ መሆናቸውን..." ያረጋግጣል የሚለው አለቦታው የገባ ቅድመ ሁኔታ ነው::

- በመሠረቱ የማንኛውም ሰው በሙስናም ሆነ በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ መሆን እና አለመሆን ማጣራት እና መወሰን የፍርድ ቤት ብቻ ሥልጣን ነው:: የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤት ለምዝገባ የሚቀርቡ ድርጅቶችን የወንጀል ተጠያቂነት እና ኃላፊነት ማጣራትና መወሰን ተግባሩ አይደለም፣ ሥልጣንም የለውም::

- መያድ ለማስመዝገብ የሚቀርቡ መሥራቾችም ሕገ መንግሥታዊ በሆነ ድንጋጌ ንፁሕ ሆኖ የመገመት መብት ስላላቸው እራሳቸውን ከሙስናም ሆነ ከሌላ ዓይነት ወንጀል ነጻ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡም ሊጠየቁ አይችሉም::

- በአጠቃላይ ድንጋጌው አለቦታው የገባና ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገለትን "በሕግ መሠረት ጥፋተኛነት እስካልተረጋገጠ ድረስ ንፁህ ሆኖ የመገመት" መብት የሚያፋልስ በመሆኑ እንዲታረም አስተያየት እናቀርባለን

- ሕግ አውጪው አካል ከዚህ ድንጋጌ በስተጀርባ ሊያስጠብቀው የሚሻው መርሕ ቢኖር፣ በአዋጁ ላይ ሊደነገግ የሚችለው ክልከላ ከዚህ በታች በተገለጸው ዓይነት ሊሆን እንደሚገባና አንቀጹም "ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች" በሚለው የአዋጁ ክፍል ስር ሊቀመጥ የሚችል መሆኑን አስተያየት እናቀርባለን::

*ከመያድ የቦርድ አባልነት እና አመራር ስለሚታገዱ ሰዎች*

*የሌላ ማናቸውም ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማናቸውም መያድ የቦርድ አባል፣ ወይም ሥራ አስኪያጅ በኢትዮጵያ ወስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ በሙስና፣ በእምነት ማጉደል ወይም በአታላይነት ወንጀል የተፈረደበት ከሆነ እራሱን ከመያድ አመራር ያገላል::*
*ማናቸውም ይህን ድንጋጌ የጣሰ ሰው የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮበት ሲፈረድበት ከብር 5,000.- (አምስት ሺ ብር) በማያንስ መቀጫ ይቀጣል::*

CGRIA

- በዚህ ዓይነት ድንጋጌ በተጠቀሱት ወንጀሎች ጥፋተኛ የሆነ ሰው ራሱን ከመያድ አመራር ማግለል ያለበት ሲሆን ይህን ተላልፎ ቢገኝም ጥፋተኛነቱ ከተረጋገጠበት በሕግ የተወሰነውን መቀጫ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል::

### 2.2.4 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ወይም ስለመከልከል

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 18 እና 19 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታ፣ ወይም ስለሚከለከልበት ሁኔታ ይደገግጋል::
የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ወይም ስለመከልከል የሚደነግጉት አንቀጾች ከዚህ በታች በቀረቡት መርሆዎች እና ነጥቦች በመመራት ተሻሽለው እንዲፃፉ አስተያየት እናቀርባለን::

- የመጀመሪያውና ዋነኛው ነጥብ የምዝገባ ጽ/ቤቱ በሕጉ ላይ በግልጽ በተመለከቱ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ምዝገባ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ መስጠት እንዳለበት በግልጽ ሊደነገግ የሚገባ ስለመሆኑ ነው::

- ይህ ሊሆን የሚገባበት ምክንያት በመሠረቱ ጥያቄው መሠረታዊ ከሆነ የመደራጀት መብት የሚመነጭና በሕግ በግልጽ ተለይተው በተደነገጉ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ሊከለከል የማይገባና ምዝገባ ጽ/ቤቱም ግዴታ ያለበት መሆኑን በግልጽ ለማመልከት ነው::

- ይኸውም መርሕ አሁን በሥራ ላይ ባለው የማህበሮች ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/59 አንቀጽ 8 ስር በግልጽ ተደንግጓል:: በዚህ ድንጋጌ መሠረት "ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ በቀረበለት ቁጥር ቀጥሎ እንደተዘረዘረው [በሕጉ የተዘረዘሩ ምክንያቶች] ሆኖ ካላገኘው በቀር ሁል ጊዜ [ሰረዝ የተጨመረ] የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል" በማለት ይደነግጋል::

- ከዚህ መረዳት የሚቻለው በ1959 ዓ.ም. እንኳን ወጥቶ የነበረው ደንብ በማህበር የመደራጀትን ደንብ በሕግ ተገቢው ጥበቃ ይደረግለት ዘንድ ከላይ የተጠቀሱትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ የምዝገባ አመልካቾችን የመመዝገብ መብት እና የመዝጋቢውን ጽ/ቤት በሕግ በግልጽ በተሰጠ ምክንያት ካልሆነ በቀር የመመዝገብ ግዴታ በግልጽ ቋንቋ ያስቀምጣል::

- አሁን የሚወጣው ሕግ በ1959 ወጥቶ በነበረ ደንብ በጠበቀ ሁኔታ የሕግ ጥበቃ ተደርጐለት የነበረውን መብት በአነሰ ሁኔታ ወይም በላላ መልኩ የሚያቀርብ እንዲሆን አይጠበቅም::
በዚህ ረገድ በአጠቃላይ አሁን የሚወጣው ሕግ እስከአሁን ድረስ በሥራ ላይ በነበሩ ደንቦች ተገቢ ጥበቃ ተደርጐላቸው የቆዩ መብቶችን የሚሸራርፍ፣ የሚቀንስ ወይም የሚያላላ እንዳይሆን የሕግ አርቃቂው ኮሚቴ ተገቢው ጥንቃቄ ያደርግ ዘንድ ለማስታወስ እንወዳለን::

CCRDA

- ስለሆነም የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ ከላይ እንደተመለከተው የምዝገባ ጽ/ቤቱ በሕጉ በግልጽ በተመለከቱ ከባድ ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ምዝገባ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ የተጠየቀውን ፈቃድ የሚሰጥ ስለመሆኑ እስከ አሁን በሥራ ላይ ባለው ደንብ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው አሁንም በዚህ አዋጅ ላይ በተመሳሳይ ቋንቋ በግልጽ እንዲቀመጥ አስተያየት እናቀርባለን::

- የምዝገባ ምስክር ወረቀት በ60 ቀናት ውስጥ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን በመርሕ ደረጃ መደንገጉ ብቻውንና በራሱ የምዝገባ ወረቀት በ60 ቀናት ለማግኘት ዋስትና እንደማይሆን ግልጽ ነው:: ለዚሁም ማስረጃው አሁን በሥራ ላይ ባለው የማህበራት ምዝገባ ደንብም የምዝገባ ምስክር ወረቀት በ60 ቀናት ውስጥ ሊሰጥ እንደሚገባ ግልጽ ድንጋጌ ቢኖርም በተግባር የሚታወቀው ሁኔታ ግን ከዚህ እጅግ የራቀ እንደነበር ይታወሳል::

- ስለሆነም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄው በቀረበ በ60 ቀናት ውስጥ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ በግልጽ ከመደንገግ በተጨማሪ ይህ በሕግ የተወሰነው ጊዜ የሚያልፍ ቢሆን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ መደንገግ ያስፈልጋል::

- ስለዚህ የምዝገባ ጽ/ቤቱ ጥያቄው ከቀረበለት ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፣ 60 ቀናት ካለፈ በኋላ በአለው የሚቀጥለው የሥራ ቀን ጊዜያዊ የምዝገባ ወረቀት እንዲሰጥና መያዱ ሥራውን ለመጀመር እንዲያስችለው እንዲደነገግና ምዝገባ ጽ/ቤቱ ጥያቄው ከቀረበለት ጀምሮ እስከ 120 ቀናት ድረስ ውሳኔ ለመስጠት ካልቻለ ግን መያዱ እንደተመዘገበ እንደሚቆጠር እንዲደነገግ አስተያየት እናቀርባለን::

- በዚህ መርሕ መሠረት ማናቸውም መያድ ለምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ መዝጋቢው ጽ/ቤት ውሳኔ ሳይሰጠው120 ቀናት ያለፈ ከሆነ መያዱ በሕግ አግባብ እንደተመዘገበ ይቆጠራል፣ ሥራውን ማካሄድ ይችላል፣ የምዝገባ ጽ/ቤቱም የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ይገደዳል ማለት ነው::

- ከላይ እንደተገለጸው የምዝገባ ጽ/ቤት የቀረበለትን ጥያቄ ላለመቀበል የሚችለው በሕጉ በግልጽ ተለይተው በተቀመጡ ምክንያቶች ብቻ ሲሆን፣ እነዚህም ምዝገባን ለመከልከል በሕጉ ሊቀመጡ የሚችሉት ምክንያቶች:-

    - በምዝገባ ማመልከቻው ውስጥ ወይም በአባሪ ሰነዶች ውስጥ የተገለጹ ፍሬ ነገሮች ሐሰት ለመሆናቸው መረጃ የተገኘ እንደሆነ፣
    - የመያዱ ዓላማ ከሕግ ውጪ ለሆነ ጉዳይ ወይም ከሞራል ውጪ ለሆነ ጉዳይ እንደሆነ፣ እና
    - የመያዱ ዓላማ ብሔራዊ አንድነትን ወይም ጥቅምን የሚነካ እንደሆነ ብቻ መሆን አለበት::

CCRDA

- የምዝገባ ጽ/ቤቱ ምዝገባ በሚከለክልበት ጊዜ ሁሉ ውሳኔውን በጽሑፍ ማስታወቅ እና ምዝገባውን የከለከለበትን በሕግ የተፈቀደ ምክንያት ከእነ ማስረጃው መግለጽ ይገባዋል::

- የምዝገባ ጽ/ቤቱ ምዝገባን በመከልከል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ወይም ምዝገባን በሕግ ከተመለከተው ጊዜ በላይ በማዘግየቱ የተነሳ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ በግልጽ ሊደነገግ ይገባል::
በምዝገባ ክልከላ ወቅት ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ ባለው የፍትሐብሔር ሕጉ የማሕበራት ድንጋጌዎች ውስጥ በቁጥር 470/2/ ሥር በግልጽ ተደንግጎ የሚገኝ ቢሆንም ረቂቅ አዋጁ በዝምታ አልፎታል::
(አዲስ እና የተሻሻለ ሕግ በማውጣት ረገድ ከነባሩ ሕግ ውስጥ ሊስተካከሉና ሊታረሙ የሚገቡ ጉዳዮች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በነባሩ ሕግ ተረጋግጠው የነበሩ መሠረታዊ መብትና ጥቅሞች ግን አዲስ ሕግ በማውጣት ሰበብ እንዳይሸራረፉ፣ እንዳይለዋወጡ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በድጋሚ በአደራ እናስታውሳለን::)

- በአጠቃላይ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ወይም ክልከላን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ከዚህ በላይ በሰፈሩት መርሆዎች እና ነጥቦች መሠረት ተስተካክለውና ተሻሽለው እንዲጸኑና፤ ምዝገባ በተከለከለ ጊዜ ሁሉ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑም በግልጽ እንዲደነገግ አስተያየት እናቀርባለን::
(የፍርድ ቤት ይግባኝ አቀራረብ ሁኔታን በሚመለከት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሌላ ክፍል በዝርዝር አስተያየት የተሰጠበት ስለሆነ አንባቢው ስለ ይግባኝ መብት የሚመለከተውን ክፍል እንዲመለከት እንጠይቃለን::)

### 2.2.5 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለሚያገለግልበት ዘመን (Validity period of the registration certificate)

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 18(2) እና 20(2) የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ለሁለት ዓመት ብቻ እንደሆነና በየሁለት ዓመቱ መታደስ እንደሚገባው ይደነግጋል::
የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊያገለግል የሚገባበትን ዘመን በተመለከተ የሕግ አርቃቂ ኮሚቴው ከዚህ በታች የተመለከተውን መርሆዎችና ነጥቦች በሚገባ አጢኖ ከላይ የተጠቀሱትን አንቀጾች እንዲታረሙ አስተያየት እናቀርባለን::

- ማንኛውም መያድ በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ መያዱ የተቋቋመበትን ዘመን የሚገልጽ ክፍል ወይም አንቀጽ አለው:: የመያድ መመስረቻ ጽሑፍ ሊይዛቸው ከሚገባቸው መረጃዎች አንዱም መያዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደተቋቋመ የሚገልጽ አንቀጽ መሆኑን በሕጉ ላይ ተመልክቷል::

CCRDA

- በመያድ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ መያዱ ለምን ያህል ዘመን እንደተቋቋመ መግለጽ የሚያስፈልግበት ምክንያት መያዱ ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ለምን ያህል ጊዜ ፀንቶ እንደሚቆይ መታወቅና መወሰን ስላለበት ነው::

- በመሆኑም ማናቸውም መያድ በምዝገባ ጽ/ቤት የምዝገባ ማመልከቻው እና የመመስረቻ ጽሑፉ ተቀባይነት አግኝቶ ከተመዘገበ በኋላ፣ የመያዱ የሕይወት ዘመን የሚወሰነው በመመስረቻው ጽሑፍ ላይ መያዱ ለምን ያህል ዘመን እንደሚቆይ በተደነገገው መሠረት ብቻ ነው::

- በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ከተመለከተው ውጪ የመያዱ የሕይወት ዘመን በምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም በሌላ በማናቸውም ዓይነት መንገድ ወይም ምክንያት መያዱ የተቋቋመበትን ዘመን ለማሳጠር ወይም ለመገደብ ማናቸውም ዓይነት የሕግ መሠረት የለም::

- ለመያዱ የሚሰጠው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊያገለግል የሚችለውና የሚገባው በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ በተመለከተው መሠረት መያዱ ለተቋቋመበት ዘመን ነው:: ስለሆነም የመያዱ መመስረቻ ጽሑፍ መያዱ ላልተወሰነ ዘመን የተቋቋመ መሆኑን የሚደነግግ ከሆነ ለመያዱ የሚሰጠው የምዝገባ ምስክር ወረቀትም ሊያገለግል የሚገባው ላልተወሰነ ዘመን ነው::

- እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ ያለው የማህበራት ምዝገባ ደንብም የሚፈቅደው ለአንድ በሕግ የተመዘገበ ማሕበር የሚሰጠው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማህበሩ ለተቋቋመበት ዘመን ያህል የሚያገለግል እንዲሆን ነው::

- የማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/59 አባሪ የሆነው ሠንጠረዥ (ለ) ሚሕበር ለመመዝገቡ የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት ዓይነት የሚደገግግ ሲሆን ማህበሩ የተመዘገበበትንና የምዝገባው ምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በሚመለከት "ማህበሩ የተቋቋመበት ዘመን" እንዲገለጽ በግልጽ ይደነግጋል::

- በዚህ መሠረት የምዝገባው ምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ማህበሩ ለተቋቋመበት ጊዜ ስለመሆኑ በ1959 ዓ.ም. በወጣው የማህበሮች ምዝገባ ደንብ እንኳን በግልጽ ተደንግጐ እያለ ረቂቅ አዋጁ የአንድን መያድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በሁለት ዓመት መገደቡ ትክክል አይደለም::

- ከላይ እንደተገለጸው በነባሩ ሕግና ደንብ መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ማህበሩ ለተቋቋመበት ዘመን በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉም ሆነ በማህበራት ምዝገባ ደንብ ላይ ስለ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እድሳት የሚያወሳ አንድም አንቀጽ የለም፣ ሊኖርም አይችልም፣ ሊኖርም አይገባም::

CCRDA

- በሥራ ላይ የነበረው ሕግና ደንብ ከዚህ በላይ የተገለጸው ቢሆንም በማሕበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ግን ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ የምዝገባ ምስክር ወረቀትን አገልግሎት ዘመን በአንድ ዓመት ብቻ በመገደብ በየዓመቱ ዕድሳት እንዲደረግ ሲጠየቅ መቆየቱ ይታወሳል::

- ይህ አሰራር አንዳችም የሕግ መሠረት የሌለውና በሥራ ላይ ካለው የማህበራት ምዝገባ ደንብ ውጪ ነው:: የመያዱ ማሕበረሰብ ጥያቄ እስከአሁን ድረስ ከሕግና ከደንብ ውጪ ሲሰራ የቆየው ተግባር እንዲቆም እንጂ ከሕግ ውጪ የሆነው ተግባር በሕግ ተደንግጐ እንዲወጣ አይደለም::

- ማናቸውም መያድ የተቋቋመበትን ዘመን በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ በግልጽ እንዲያስቀምጥ ተጠይቆና በዚሁ መሠረትም ፈጽሞ እያለ፣ በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ ከተመለከተው ውጪ መያዱ የተቋቋመበትን ዘመን በምዝገባ የምስክር ወረቀት ለመገደብ የሚቻልበት አንዳችም የሕግ ምክንያት የለም::

- ሰዎች መሠረታዊ የሆነ ሕገመንግሥታዊ የመደራጀት መብታቸውን በመጠቀም በሥራ ላይ ያዋሉት የመደራጀት መብት በመዝጋቢው ጽ/ቤት ለሁለት ዓመት ብቻ እንደተፈቀደ መብት ተደርጐ መገደብ አይችልም::

- ሰዎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው የመሰረቱት ድርጅት የተቋቋመበትን ዘመን የሚወስኑት እራሳቸው የማህበሩ ወይም የድርጅቱ መሥራቾች እንጂ፣ መዝጋቢው ጽ/ቤት የመስራቾቹን የመደራጀት መብት በዓመት ወይም በሁለት ዓመት በማለት እየገደበ ሊሰጣቸው አይችልም፣ አይገባም፣ ሕገ መንግሥታዊም አይደለም::

- በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ መያዱ የተቋቋመበት ዘመን መግለጹ ከዚህ ውጪ ሌላ ጠቀሜታ እና አገልግሎት የለውም:: አንድ ድርጅት የተቋቋመበትን ዘመን በመመስረቻው ጽሑፍ እንዲገልጽ የተፈለገው ለዚህ ዓላማ ነው እንጂ ይህን ዓላማ የማያሳካ ከሆነ ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዘመን በመመስረቻ ጽሑፉ መግለጽ እንግዲያውስ ለምን አስፈለገ?

- ስለዚህም በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁሉ የመያድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በተወሰኑ ዓመታት እንዲገደብ ማድረጉ የሕግ ድጋፍ የሌለው፣ እስከ አሁንም በሥራ ላይ ባለው ደንብ ያልተፈቀደ፣ መሠረታዊ ለሆነው የመደራጀት መብት መርሕ ተቃራኒ የሆነ፣ ከመያዶች የረጅም ጊዜ የልማት አጋርነት ባሕሪ ጋር የማይሄድ፣ እና የመያድን ነጻ ተቋምነት የሚቃረን በመሆኑ የሕግ አርቃቂ ኮሚቴው ጉዳዩን በጥሞና አጢኖ እንዲያርመው አስተያየታችንን እናቀርባለን::

CCRDA

- ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለማስታወስ የምንወደው የመያድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ በተመለከተው ዘመን መሠረት እንዲሆን መደረጉ መያድ በሕጉ መሠረት ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴና የሒሳብ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታውን የሚያስቀር አለመሆኑንና የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤትም በሕግ በተመለከተው ዓይነት በማናቸውም ጊዜ ተገቢውን ቁጥጥር ከማድረግ የሚያግደው አለመሆኑን ነው::

- ከዚህ በላይ ስለመያድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመን የቀረቡት መሠረታዊ መርሆዎች ትክክለኛ እና ሕጋዊ መሠረት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ የሚከተለውን ሐሳብ በአማራጭነት እናቀርባለን::

- ማናቸውም መያድ በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ ለተመለተው ዘመን ያህል የሚያገለግል የምዝገባ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት ለተወሰነ ዘመን በእንቅስቃሴው ላይ ክትትል ሊደረግበት የሚገባበት ሕጋዊ ምክንያት አለ የሚባል ቢሆን የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ዘመን ከዚህ በታች በተመለከተው ዓይነት እንዲሆን በአማራጭ ለማሰብ ይቻላል:: ይኸውም:-

    - የመጀመሪያው ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለሶስት ዓመት እንዲያገለግል፣

    - ከመጀመሪያው ሶስት ዓመት በኋላ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ለቀጣዩ አምስት ዓመት እንዲያገለግል እንዲታደስ እና

    - ከአምስት ዓመቱ የዕድሳት ዘመን በኋላ የመያዱ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ ለተመለከተው ዘመን ያህል እንዲያገለግል ሆኖ እንዲሰጥ (የመመስረቻ ጹሑፉ መያዱ ላልተወሰነ ዘመን መቋቋሙን የሚገልጽ ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱም ላልተወሰነ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይ መሆኑ ተገልጾ እንዲሰጥ) እንዲደረግ አስተያየት እናቀርባለን::

### 2.2.6 የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 22 የመያድ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመያድ ምዝገባ ጽ/ቤት ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ስለመቻሉ ይደነግጋል::
የአዋጁ ምዕራፍ አንድ ክፍል ሶስት ድንጋጌዎች "ምዝገባን" የሚመለከቱ ስለሆነ ስለ እገዳ እና መሰረዝ ጉዳይ በዚህ ክፍል መነሳቱ ያለቦታው ነው:: የረቂቅ አዋጁ ክፍል አምስት "ስለመያድ መፍረስ፣ መሠረዝ እና ሒሳብ ማጣራት" የሚደነግግ በመሆኑ የመፍረስ እና የመሰረዝ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሙሉ በዚሁ ክፍል መጠቃለላቸው ተገቢ ይሆናል::

CCRDA

ስለሆነም በዚህ ጽሑፍም የመያድን መፍረስና መሰረዝ ጉዳይ በሚመለከት ከመያድ ማሕበረሰብ የሚቀርበው አስተያየት እና የማሻሻያ ሐሳቦች በዚያው ክፍል ተጠቃልለው የቀረቡ ስለሆነ አንባቢው "ስለ መያድ መፍረስ፣ መሰረዝ እና ሒሳብ ማጣራት" የሚመለከተውን ክፍል እንዲመለከት እንጠይቃለን::

## 3. ክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ፤ ስለ መብቶችና ግዴታዎች

### 3.1 ስለ መርሕ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 23 የመያድን መብትና ግዴታ ዋነኛ መርሕ ይደነግጋል:: ይኸውም "የመያዱ መብቶችና ግዴታዎች የአባላቱ መብቶችና ግዴታዎች አይደሉም" የሚል ነው::

መርሕን በሚመለከት በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 451 ሥር የተደነገገው በተሟላ መልኩ የተቀመጠ ስለሆነ አሁንም በአዋጁ ላይ በዚሁ በተሟላ መልኩ እንዳለ እንዲቀመጥ አስተያየታችንን እናቀርባለን::
ይኸውም:-

- መያድ በውስጡ ከአሉት አባላት የተለየና የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ስለመሆኑ፣
- የመያዱ መብቶችና ግዴታዎች የአባሎቹ መብቶችና ግዴታቸው አለመሆኑ፣ እና
- እንዲሁም የመያዱ አባሎች መብቶችና ግዴታዎች የመያዱ መብቶችና ግዴታዎች አለመሆኑ ነው::

### 3.2 ስለ ስም

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 24 (1) "ማናቸውም መያድ ከዓላማው ጋር የተያያዘ ስም ሊኖረው ይገባል" የሚለው ድንጋጌ ውስጥ "ከዓላማው ጋር የተያያዘ" የሚለው ሐረግ የግድ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲታረም እናስታውሳለን::

### 3.3 ስለ ሕጋዊ ሰውነትና ችሎታ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 25 የመያድን ሕጋዊ ሰውነት እና ችሎታ ይደነግጋል:: ይህ አንቀጽ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መርሆዎች እና ነጥቦች መሠረት ተሻሽሎ እንዲዋፍ አስተያየታችንን እንደሚከተለው እናቀርባለን::

CGRDA

- የመያድ ሕጋዊ ሰውነትና ችሎታ የሚመለከተው ድንጋጌ በመጀመሪያ ደረጃ ዋነኛ የሆነውን መርህ በግልጽ በመደንገግ ሊጀምር ይገባዋል። በዚህ ረገድ የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 454(1) ይህን ዋነኛ መርሕ በተሟላ መልኩ የሚያስቀምጠው ስለሆነ አዋጁም በተመሳሳይ ቋንቋ መርሁን በመደንገግ ሊጀምር ይገባዋል። ይኸውም "መያድ ከዐይነቱ ጋር የሚስማሙትን የብሔራዊ ኑሮ ተግባሮችን ሁሉ መፈጸም ይችላል" (NGO may perform all civil acts which are consistent with its nature) የሚል ነው።

- ከዚህ በላይ የተገለጸው ዋነኛ መርሕ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመያዱ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ዋነኛ የሕግ ችሎታዎችንም በዝርዝር ማመልከቱ ጠቃሚ በመሆኑ በዚህ ረገድ በአንቀጽ 25(3) የተመለከተው በግልጽ የንብረት ባለቤት የመሆን ችሎታን (the right of ownership) እና በዚህ መሠረትም ንብረቱን የማስተዳደር፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ በስጦታ የማስተላለፍ መብቶችን በግልጽ ለይቶ እንዲያመለክት እናስታውሳለን።

- መያድ የልማት አጋር እንደመሆኑ መጠን ለዓላማዎቹ መሳካት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ሁሉ በሕግ አግባብ የመጠየቅና የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በዚህ መብትና ግዴታን በሚደነግገው ክፍል ሊደነገግ የሚገባ መሆኑን አስተያየት እናቀርባለን።

### 3.4 ስለ ሌሎች ግዴታዎች እና ክልከላዎች

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 26 "ሌሎች ግዴታዎችና ክልከላዎች" በሚል ርዕስ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (5) የተመለከቱትን ክልከላዎች በሚመለከት ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት እናቀርባለን።

- በአንቀጽ 26(1) ድንጋጌ መሠረት "ማንኛውም መያድ እንደ ጤና እና ትምህርት የመሰሰሉትን የሙያ ነክ ተግባራት ለማከናወን ከምዝገባ በፊት ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት" በማለት ይደነግጋል።

- በቅድሚያ ምዝገባን የሚመለከቱ ማናቸውም ሁኔታዎች "ምዝገባን" በሚመለከተው የአዋጁ ክፍል ሊካተቱ የሚገባ ስለሆነ ይህ ንዑስ አንቀጽ ከሕግ ማርቀቅ (drafting) ቴክኒክ አንጻር አለቦታው የተቀመጠ መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን።

- በዚህ ጽሑፍ ምዝገባን በሚመለከተው ክፍል የመያድ ምዝገባ የመደራጀትን መብት ሊያግድ በሚችል ቅድመ ሁኔታ ሊገደብ እንደማይገባው በተገቢው መጠን ተገልጿል። (አንባቢው ምዝገባን የሚመለከተውን የዚህን ጽሑፍ ክፍል እንዲመለከት እንጠይቃለን)

ECRDA

- ምዝገባን በሚመለከተው የዚህ ጽሑፍ ክፍል ከተገለጹት ነጥቦችና መርሆዎች በተጨማሪ በአንቀጽ 26(1) የተመለተው ክልከላ ተገቢ አለመሆኑን እየገለጽን የሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ እንዲያርመው እንጠይቃለን::
- መያድ የሚመሰርቱ ሰዎች ለሚመሰርቱት መያድ ሥራዎች የሙያ ብቃት ያላቸው መሆን አለመሆኑ በሕገመንግሥታዊ የመደራጀት መብታቸው ላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ተቆጥሮ ምዝገባን ሊያስከለክል የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም::
- አንድ በሕጋዊ መንገድ የተቋቋመና የተመዘገበ መያድ ለሚሠማራበት ሥራዎች ተገቢው የሙያ ብቃት ያለው የሰው ሃይል እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶች ያሉት መሆን አለመሆኑ መሠረታዊ ከሆነው የመደራጀትና የመመዝገብ መብት ጋር የሚያያዝ ሳይሆን መያዱ ወደ የዕለት ተዕለት ሥራው ሲገባ (at the operational activity level) በዚያ ደረጃ በሚመለከተው አካል የሚነሳ ጥያቄ ነው::

- ማናቸውም መያድ ገና ሳይቋቋምና ሳይመዘገብ ሊሰማራበት ስላቀደው ሥራ የሚሆኑ ባለሙያዎችን መቅጠር፣ ንብረት ማፍራትና የመሳሰሉትንም ተግባራት ለማከናወን በሕግ ስለማይፈቀድለት፣ ጥያቄው ያለቦታው የተነሳ ነው:: ለምሳሌም ያህል አንድ ለድህ የሕብረተሰብ ክፍል የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያቅድ መያድ ቢመሠረት፣ የሕክምና አገልግሎቱን በተፈቀደላቸው ባለሙያዎችና ስለሕክምና አገልግሎት በተደነገጉ መስፈርቶች (standards) መሠረት ለመስጠት መቻሉ መያዱ ከተመሠረተ በኋላ ታይቶ የሚወሰን እንጂ ገና መያዱ ሳይቋቋምና ሳይመሰረት የመያዱ መሥራቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሊጠየቁም ሊሰጡም አይችሉም::

- የአንድ መያድ መሥራች አባላትም የግድ በመያዱ የተግባር ሥራዎች ላይ ባለሙያዎች እንዲሆኑ አይጠበቅባቸውም:: መያድ የሚመሰረተው በበጎ ፈቃደኛ ሰዎች አንድ ለጠቅላላው ጥቅም የሆነ ዓላማ ለማሳካት በመሆኑ የመያዱ መቋቋምና መመዝገብ፣ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ሊገደብ አይችልም::

- በአንቀጽ 26(5) ድንጋጌ መሠረት መያድ በሚፈርስበት ወቅት ንብረቱ ተመሳሳይ ዓላማ ወደአለው መያድ በመዝጋቢው ጽ/ቤት በኩል እንደሚተላለፍ ተመልክቷል::
ይህ የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ ካለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 467 ድንጋጌ ውጪ በመሆኑ የሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 467 የተመለከተውን መሪ ሀሳብ በመከተል ከዚህ በታች በተመለከተው ዓይነት እንዲሻሻል አስተያየት እናቀርባለን::
    - በመመስረቻ ጹሑፍ ወይም በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ካልተመለከተ፣ ወይም የመያዱ የበላይ የሥልጣን አካል የፈረሰው ወይም የተሰረዘው መያድ ንብረት በሕጋዊ መንገድ ለሌላ ሕጋዊ እና ተመሳሳይ ዓላማ እንዲተላለፍ ካላደረገ፣ የፈረሰው ወይም የተሰረዘው መያድ ንብረቶች በመዝጋቢው ጽ/ቤት በኩል ተመሳሳይ ዓላማ ለሚያራምዱ መያዶች ይተላለፋል::
    - መያዱ የፈረሰው ወይም የተሰረዘው በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሆን የማህበሩ የበላይ የሥልጣን አካል ስለንብረቱ መተላለፍ ሁኔታ ለመወሰን አይችልም::

CCRDA

## 4. ክፍል አራት ፤ ስለ ሪፖርትና ቁጥጥር (አንቀጽ 27- 30)

### 4.1 ስለ መሠረዝ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 28(2) መዝጋቢው ጽ/ቤት ማናቸውም መያድ በሥራ ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚያወጣው ማስታወቂያ መሠረት መያዱ ስለእንቅስቃሴው በጽሑፍ የተደገፈ ሪፖርት ካላቀረበለት የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለመሠረዝ እንደሚችል ተደንግጓል::
ከዚህ በላይ በዚህ ጽሑፍ ክፍል ሁለት ቁጥር 2.2.6 ሥር እንደተመለከተው የመያድ መፍረስ፣ መሰረዝ እና ሒሳብ ማጣራት በተመለተ በዚህ ጽሑፍ በሌላ ክፍል አስተያየት የቀረበበት ስለሆነ አንባቢው አሁንም ይህን ክፍል እንዲመለከት እንጠይቃለን::

### 4.2 ስለ አዲትና ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 29 "የእያንዳንዱ መያድ ሂሳብ በተመዘገበ የውጭ አዲተር በየዓመቱ መመርመር" እንዳለበትና ሪፖርቱም ከዓመታዊ የፋይናንስ አጠቃቀምና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ጋር ለመዝጋቢው ጽ/ቤት እና የብቃት ማረጋገጫ ለሰጠው መ/ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል::

ሆኖም ዓመታዊ የገንዘብ እንቅስቃሴያቸው አነስተኛ የሆኑ መያዶችን በውጭ አዲተር ሒሳባቸው እንዲመረመር ማድረግ አስፈላጊ ባለመሆኑና ከወጪም አንፃር ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ዓመታዊ የገንዘብ እንቅስቃሴያቸው ብር 100,000.- (አንድ መቶ ሺ ብር) እና ከዚያ በታች የሆነ መያዶች ከዚህ ግዴታ ነጻ እንዲሆኑና እንደአስፈላጊነቱ መዝጋቢው ጽ/ቤት በሚያደርገው ምርመራ ሒሳባቸው ሊጣራ የሚችል መሆኑን በሚገልጽ መንገድ ድንጋጌው ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

### 4.3 ስለ ልዩ ምርመራ

አንቀጽ 30 መዝጋቢው ጽ/ቤት ሊያካሂድ ስለሚችለው ልዩ ምርመራና በዚህ የምርመራ ውጤት መሠረትም "አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድ" እንደሚችል ይደነግጋል::
ይህን የልዩ ምርመራ የሚመለከተው ድንጋጌ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች መሠረት ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

- በአንቀጽ 30(1) ድንጋጌ መሠረት መዝጋቢው ጽ/ቤት ልዩ ምርመራ እንዲካሄድ የሚያደርገው "... የሪፖርቱን ትክክለኛነት ሲጠራጠረው ወይም ሕገወጥ ተግባር ተፈጽሞበታል የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው..." እንደሆነ ተመልክቷል::

- ይህ ድንጋጌ አሁን በአለበት መልኩ ሰፊ ክፍተት ያለው፣ ሀሳባዊ አሠራርን የሚጋብዝና ያለአግባብ ለመጠቀምም በር የሚከፍት በመሆኑ "ጥርጣሬ ሲኖር" በሚል የተቀመጡት ሐረጐች እንዲታረሙና "በቂ ማስረጃ ሲገኝ" በሚል እንዲተኩ አስተያየት እናቀርባለን::

CCRDA

- በአንቀጽ 30(3) "መዝጋቢው ጽ/ቤት በምርመራ ውጤቱ ላይ በመመሥረት አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል" በማለት ይደነግጋል። ይህ ለምዝገባ ጽ/ቤቱ በሕግ በግልጽ ተለይቶ ያልታወቀ ሥልጣን የሚሰጥና ያለአግባብ ለመጠቀምም ሰፊ በር የሚከፍት ስለሆነ እንዲታረም እንጠይቃለን።

## 5. ክፍል አምስት፤ ስለ መያድ መፍረስ፣ መሠረዝ እና ሒሳብ ማጣራት (አንቀጽ 31- 40)

### 5.1 መያድ ስለሚፈርስባቸው ሁኔታዎች

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 31 – 33 መያድ በፈቃደኝነት ወይም በግዴታ ሊፈርስ ወይም ሊሰረዝ ስለሚችልበት ሁኔታዎች ይደነግጋሉ።

በፈቃደኝነት የመፍረስ ሁኔታ በአንቀጽ 32 ድንጋጌ መሠረት በመያዱ የበላይ ሥልጣን አካል ውሳኔ መሠረት መፍረስን የሚመለከት ሲሆን በግዴታ መፍረስ ደግሞ በአንቀጽ 33 መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስን ወይም በመዝጋቢው ጽ/ቤት ውሳኔ መሠረዝን የሚመለከት ነው።

በመዝጋቢው ጽ/ቤት ውሳኔ የመሠረዝ ሁኔታም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 22 ስር ተመልክቷል። አንቀጽ 22 ስለ መያድ መሠረዝ ብቻም ሳይሆን ስለመያድ መታገድም ይደነግጋል።

የመያድን መፍረስ፣ መሰረዝ እና መታገድ በሚመለከት በአዋጁ ውስጥ ስለተመለከቱት ድንጋጌዎች የመያድ ማሕበረሰብ ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት እያቀረበ የአዋጁ ድንጋጌዎችም ከዚህ በታች በተሰጠው አስተያየት መሠረት ተሻሽለው እንዲፃፉ ይጠይቃል።

- መያድ በመዝጋቢው ድ/ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲፈርስ የሚፈቅድ ሕግ መኖሩ የዘርፉን ነፃነት ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ ነው።

- መያድ በሕጋዊ መንገድ ከተቋቋመና ሕጋዊ ሰውነት ከአገኘ በኋላ፤ ይህ በሕግ አግባብ የተገኘ ሕጋዊ ሰውነት ሊፈርስ የሚችልበትና የሚገባበት መንገድ አንድም በራሱ በድርጅቱ የበላይ የሥልጣን አካል ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ውሳኔ አሊያም በበቂ የሕግ ምክንያቶች በፍርድ ቤት ውሳኔ ብቻ ነው።

- ከእነዚህ ሁለት መንገዶች ውጪ ሕጋዊ ሰውነት የተጐናጸፈ ተቋም በአንድ መንግሥታዊ አስተዳደራዊ አካል ሕጋዊ ሰውነቱን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊነጠቅ የሚችል ከሆነ መሠረታዊ የሆነው ሕገመንግሥታዊው የመደራጀት መብት የሕግ ጥበቃ አልተደረገለትም ማለት ነው።

- ሰዎች ሕገመንግሥታዊ የሆነ የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው የመሠረቱት ድርጅት ሊታገድ፣ ሊፈርስ ወይም ሊሰረዝ የሚችለውና የሚገባው በበቂ የሕግ ምክንያቶችና ገለልተኛ በሆነ የነጻ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ብቻ ነው።

CCRDA

- ሕግ አውጪው አካል በአገራችን ውስጥ ነጻ፣ ጠንካራ እና ገለልተኛ የሆነ የሲቪል ማሕበረሰብ እንዲጐለብት ፅኑ እና ቁርጠኛ አቋም ካለው፤ የመያድ መፍረስ ወይም መታገድ ሥልጣን ለፍርድ ቤት ብቻ መስጠት አለበት::

- ማናቸውም መያድ ሊፈርስ ወይም ሊታገድ የሚገባበት በቂ የሕግ ምክንያት አለ ብሎ መዝጋቢው ጽ/ቤት በአመነ ጊዜ ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርቦና እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ የተጠየቀውም ድርጅት የበኩሉን መከራከሪያ አቅርቦ ጉዳዩ በነፃ የዳኝነት መድረክ ብቻ መወሰን ይገባዋል::

- አንድ መያድ ሊፈርስ ወይም ሊታገድ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጥያቄ በራሱ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ (justiciable matter) ነው::
በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 መሠረት "በፌዴራልም ሆነ በክልል [መንግሥት] የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ" [ሠረዝ የተጨመረ] መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል::

- በመሆኑም በአንድ በፍርድ ሊወሰን በሚገባ መሠረታዊ የመብት ጥያቄ ላይ በሕገ መንግሥቱ ለፍርድ ቤቶች ብቻ የተሰጠውን ሥልጣን በመንጠቅ በመሠረታዊ የመብት ጥያቄ ላይ አስተዳደራዊ አካል አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት መደረጉ ከሕገ መንግሥቱ ውጪ (un constitutional) ነው::

- በተለይም ይህ ረቂቅ ሕግ በፌዴራሉ የፍትሕ ሚኒስቴር አማካኝነት የሚዘጋጅ በመሆኑ የፌዴራሉ ፍትሕ ሚኒስቴር መ/ቤት በዚህ ረገድ ለሕግ የበላይነት፣ ለሕገመንግሥታዊነት፣ ለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መከበር እና ለሰዎች መሠረታዊ መብቶች መጠበቅ በጽናት በመቆም እነዚህን መርሆዎች የሚያስጠብቅ ሕግ እንዲወጣ እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

- ከዚህ በላይ የተዘረዘረው መርሕ በሙሉ ትክክለኛና ሕጋዊ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ መያድ በመዝጋቢው ጽ/ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊፈርስ የሚገባበት በቂ የሕግ ምክንያቶች አሉ የሚባል ቢሆን፤ መያድ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰረዝ የሚችለው በሕጉ ላይ አስቀድሞ በግልጽ በተደነገጉ ሁኔታዎች እና እጅግ ከፍተኛ በሆኑ የሕግ መጣስ ምክንያቶች ብቻ ሊሆን ይገባዋል::

- በእንደዚህ ዓይነቱ አስተዳደራዊ ውሳኔም ሁል ጊዜም በውሳኔው ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደተጠበቀ መሆኑ በግልጽ ሊደነገግ ይገባል:: (በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ያለውን የይግባኝ አቀራረብ በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ ይግባኝን በሚመለከተው ክፍል በዝርዝር የተመለከተ ስለሆነ አንባቢው ይህንኑ ክፍል እንዲመለከት እንጠይቃለን::)

- ስለሆነም በአጠቃላይ የመያድን መፍረስ፣ መሰረዝ፣ ወይም መታገድ የሚመለከቱት የአዋጁ ልዩ ልዩ ድግጋጌዎች ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ተሻሽለው እንዲፃፉ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

CGRDA

### 5.2 በፈቃደኝነት ስለ መፍረስ ሁኔታ

አንቀጽ 32 መያድ በፈቃደኝነት ስለሚፈርስበት ሁኔታ "በመመስረቻ ጽሑፉ በተመለከቱት ሁኔታዎች በጠቅላላው ጉባዔ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ ውሳኔ መያዱን ማፍረስ ይቻላል" በሚል ይደነግጋል:: ማናቸውም መያድ በፈቃደኝነት ሊፈርስ የሚችልበትን ሁኔታ የመያዱ መሥራች አባሎች በመያዱ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ለመደንገግ የሚችሉ ስለሆነ አንቀጽ 32 ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት እንዲሻሻል አስተያየት እናቀርባለን::

- በመያዱ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም መተዳደሪያ ደንቡ ከፍ ያለ የድምፅ ብልጫ ካልተወሰነ በቀር በመያዱ የበላይ ሥልጣን አካል ሁለት ሶስተኛ የድምፅ ብልጫ ውሳኔ መያዱን ማፍረስ ይቻላል::

### 5.3 ስለ ሒሳብ ማጣራት

በአንቀጽ 35(3) ስር "... ፍርድ ቤቱ... ማናቸውም ከሒሳብ ማጣራቱ ሥራ ጋር ያልተገናኙ ሥራዎች እንዳይካሄድ አግዶ የእገዳውን የመጀመሪያና የመጨረሻ ቀን በመጥቀስ ለመዝጋቢው ጽ/ቤት ይልካል" የሚለው ፍርድ ቤቱ ለዳኝነት የቀረበለትን ጉዳይ እንዴት እንደሚያስተናግድ ትዕዛዝ የሚሰጥ ስለሚመስል የሕጉ አርቃቂ ኮሚቴ አሻሽሎ እንዲጽፈው ለማስታወስ እንወዳለን::

### 5.4 ስለ መያድ መለዋወጥ እና መቀላቀል

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 39 እና 40 ስለ መያድ መዋሃድ እና መለያየት ሁኔታዎች ይደነግጋል:: እነዚህ የመያድን መዋሃድና መለያየት የሚመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚገኙት ስለ መያድ መፍረስ፣ መሠረዝ እና ሒሳብ ማጣራት በሚደነግገው የአዋጁ ክፍል አምስት ውስጥ ነው::

የመያድ መለዋወጥ እና መቀላቀልን (Conversion and Amalgamation) የሚመለከቱት ድንጋጌዎች አሁን በተቀመጠበት መልኩ ያለቦታው ሆኖ ስለሚታይ ስለ መያድ መለዋወጥ እና መቀላቀል ከአዋጁ ክፍል አምስት ቀጥሎ እራሱን የቻለ አንድ ክፍል እንዲሆንና በዚህ ክፍል ውስጥም የመያድ መዋሃድ፣ የመያድ መለያየት እና የውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ መለወጥ ድንጋጌዎችን እንዲያካትት ሆኖ እንዲቀረጽ አስተያየት እናቀርባለን:: በዚህ ክፍል ውስጥም የመያድ መዋሃድን፣ መለያየትንና ከውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድነት መለወጥ አስመልክቶ የሚከተሉትን አስተያየቶች እናቀርባለን::

#### 5.4.1 ስለ መያድ መዋሃድ

- በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 39 ስር የተመለከተው መዋሃድ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ድርጅቶች አዲስ ድርጅት በመፍጠር የሚቀላቀሉበትና (amalgamation by the formation of a new organization) የተቀላቀሉት ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች በመቀላቀሉ ወደተፈጠረው አዲስ ድርጅት የሚተላለፍበት ሁኔታ ነው::

CCRDA

- ሆኖም መቀላቀል (Amalgamation) በዚህ ዓይነት ብቻ የተወሰነ አይደለም:: በአጠቃላይ ሁለት ዓይነት የመቀላቀል ሁኔታዎች ሲኖሩ አንደኛው ከላይ በተገለጸው ዓይነት የሚፈጸመው ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት አንዱ ድርጅት ሌላውን ድርጅት በመጠቅለል (merger by take over) የሚፈጸም ነው:: በዚህ ዓይነቱ መቀላቀል የአንደኛው ድርጅት መብትና ግዴታዎች ወደ ጠቅላዩ ድርጅት (the organization taking over) ይተላለፉሉ፣ የተጠቅላዩ ድርጅት (the organization taken over) ሕጋዊ ሕልውናም ይከስማል::

- ይህ ሁለተኛው ዓይነት መቀላቀል በብዛት በንግዱ ዓለም ድርጅቶች የተለመደ በመሆኑ አግባብነቱ ለንግድ ድርጅቶች ብቻ ቢመስልም መርሆዎቹና የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓቱ ለማናቸውም ዓይነት ድርጅት ተፈጻሚነት ያለው ነው:: ከአሠራር ቅልጥፍና እና ከወጪም አንጻር ይበልጥ ተግባራዊ የሚሆነው የዚህ ዓይነቱ የመጠቅለል ውሕደት ነው::

- የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ውሕደቶች ውስጥ አንደኛውን ዓይነት ብቻ ስለሚጠቅስና ይልቁንም በተግባር የሚሠራበትን የመቀላቀል ዓይነት የማይጠቅስ በመሆኑ ድንጋጌው ሁለቱንም ዓይነቶች መቀላቀል በሚያንጸባርቅ መልኩ ተሻሽሎ እንዲጸፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

- አንቀጽ 39(3) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መቀላቀል በተመለከተ በመዝጋቢው ጽ/ቤት አማካኝነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ሊጸድቅ እንደሚገባው ይደነግጋል::
ሆኖም የዚህ ዓይነቱ መዋሃድ በፍርድ ቤት መጽደቅ በተለይ ለበጎ አድራጐት ድርጅት ብቻ የሚያስፈልግበት በቂ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ከላይ የተገለጸው የመዋሃድ ሥርዓት ለማናቸውም ዓይነት መያድ ተፈጻሚ እንዲሆን አስተያየት እናቀርባለን::

- የማንኛውም መያድ መዋሃድን በተመለከተ የውሕደቱ ውሳኔ በሚዋሃዱት መያዶች በእያንዳንዳቸው ሊወሰን የሚገባው ስለመሆኑ፣ የውሕደቱ ስምምነት ለመዝጋቢው ጽ/ቤት ሊቀርብ የሚገባው ስለመሆኑ፣ መዝጋቢው ጽ/ቤት ስለ ውሕደቱ ሁኔታ ማስታወቂያ ሊያወጣ የሚገባ ስለመሆኑ እና የውሕደቱ ስምምነት በመዝጋቢው ጽ/ቤት ሲፀድቅ ውሕደቱ እንደተፈጸመ እንደሚቆጠርና በውሕደቱ ሕልውናው የጠፋው (የጠፉት) መያዶች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመዝጋቢው ጽ/ቤት እንደሚመለስ ሊደነገግ የሚገባው መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን::

CCDA

### 5.4.2 ስለመያድ መለያየት

አንቀጽ 40 ስለመያድ መለያየት የሚደነግግ ቢሆንም የመለያየቱን ሥነ ሥርዓት (Procedure) እና አፈጻጸሙን የማይዘረዝር በመሆኑ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች በሚያካትት መልኩ ተሻሽሎ እንዲጸፍ አስተያየት እናቀርባለን::

- የመለያየቱ ስምምነት እና ተለይቶ የሚወጣው አዲስ መያድ የመተዳደሪያ ደንብ ለመዝጋቢው ጽ/ቤት የሚቀርብ ስለመሆኑ፣
- እንዲሁም ተለይቶ የሚወጣው አዲስ መያድ የመጀመሪያው የቦርድ አባላት ስም ዝርዝር እና ለወደፊቱ የቦርድ አባላት ስለሚመረጡበት ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ሊመለከት የሚገባ ስለመሆኑ፣
- የመለያየቱ ስምምነት በመዝጋቢው ጽ/ቤት ሲጸድቅ በመለየቱ ሒደት ለተፈጠረው አዲስ መያድ መዝጋቢው ጽ/ቤት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጥ ስለመሆኑ ሊደነገግ እንደሚገባ ለማስታወስ እንወዳለን::

### 5.4.3 የውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ መለወጥ

ረቂቅ አዋጁ የውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ ሊለወጥ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚደነግግ አንቀጽ የለውም:: ይሁንና የውጭ አገር መያዶች ወደ አገር ውስጥ መያድነት የመለወጥ ሁኔታ ከዚህ በፊትም የነበረ ክስተት እና አሁንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ በመሆኑ አዋጁ ይህን ጉዳይ የሚመለከት ድንጋጌዎች በዚህ ስለ "መለወጥ እና መቀላቀል" በሚመለከተው ክፍል ውስጥ ሊያካትተው ይገባል::

የውጪ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ የመለወጥ ሁኔታ በሚከተሉት ነጥቦች መሠረት እንዲመራ አስተያየት እናቀርባለን::

- በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚሰራ የውጭ አገር መያድ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ወደ አገር ውስጥ መያድ ሊለወጥ የሚችል ስለመሆኑ፣
- የውጭ አገር መያድ ወደ አገር ውስጥ መያድ መለወጥ ሁኔታ በመያዱ የበላይ ሥልጣን አካል ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣
- የውጭ አገሩ መያድ የበላይ ሥልጣን አካል ውሣኔ፣ የመለወጡን ሁኔታ የሚገልጸው ዝርዝር ስምምነት እና በመለወጡ ሒደት የሚፈጠረው የአገር ውስጥ መያድ የመተዳደሪያ ደንብ ለመዝጋቢው ጽ/ቤት ቀርቦ ሊጸድቅ የሚገባ ስለመሆኑ፣

CGRDA

- በመለወጡ ሒደት የሚፈጠረው የአገር ውስጥ መያድ መተዳደሪያ ደንብ የመያዱን የመጀመሪያ ቦርድ አባላት ስም ዝርዝር እና የወደፊት ቦርድ አባላት የሚመረጡበትን ሥነ ሥርዓት ሊገልጽ የሚገባ መሆኑን፣

- የመለወጡን ሁኔታ የሚገልጸው ዝርዝር ስምምነት ወደተለወጠው የአገር ውስጥ መያድ የተላለፉትን ንብረቶች ዝርዝር ሊያመለክት የሚገባ ስለመሆኑ፣

- የውጭ አገሩ መያድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ያሉት መብትና ግዴታዎቹ በመለወጡ ሒደት ወደተፈጠረው የአገር ውስጥ መያድ የሚተላለፍ ስለመሆኑ፣

- የመለዋወጡ ስምምነት ሲጸድቅ የምዝገባ ጽ/ቤቱ ለአገር ውስጥ መያዱ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንደሚሰጥና በመለዋወጡ ሒደት በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው ሕልውናው ቀሪ የሚሆነው የውጭ አገር መያድ የምዝገባ ምክስር ወረቀት የሚመለስ ስለመሆኑ በአዋጁ ሊደነግግ ይገባል።

## III ምዕራፍ ሁለት ፤ ስለ ማህበራት (አንቀጽ 41- 65)

የረቂቅ አዋጁ ምዕራፍ ሁለት ስለ ማህበራት መቋቋም፣ ስለ የማህበር መመስረቻ ጽሑፍ ይዘት፣ ስለ ማህበር አባሎች፣ ስለ ማህበር አስተዳደርና አወቃቀር፣ ስለማህበሩ አካላት ሥልጣንና ተግባር፣ ስለ ስብሰባና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንቦች፣ ስለ ውሳኔ አሰጣጥ ደንቦች እና ስለ ማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር ይደነግጋል።
የምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎችን በአጠቃላይ በሚመለከት ከዚህ በታች የተዘረዘረውን አስተያየት እያቀረብን በአስተያየቱ መሰረት ማሻሻያዎች እንዲደረጉ እንጠይቃለን።

1. ሁለት የማህበር ዓይነቶችን በተመለከተ

- አንድ ማህበር በዐይነቱ የአባላት ማህበር (membership organization) ወይም አዲስ አባላት የማይቀበል ማህበር (non-membership organization) ሊሆን እንደሚችል የታወቀና በረቂቅ አዋጁም የተመለከተ ጉዳይ ነው።

- በረቂቅ አዋጁ ስለ ማሕበራት የተቀመጡት ድንጋጌዎች በሙሉ የአባላት ማሕበርን እሳቤ በማድረግ የተሰሩና ቀጥተኛ አግባብነታቸውና ተፈጻሚነታቸው ለአባላት ማህበሮች የሆነ ነው።

- የአባላት ማህበር እና አዲስ አባላትን የማይቀበል ማህበር ድርጅታዊ አወቃቀራቸው የተለያየ መሆኑ ይታወቃል። ለምሳሌም የአባላት ማህበር ከፍተኛውና የበላይ የሥልጣን አካሉ የአባላት ጠቅላላ ጉባዔ ሲሆን፤ አዲስ አባላትን የማይቀበል ማህበር ግን ጠቅላላ ጉባዔ የሚባል አካል ስለማይኖረው የማህበሩን ከፍተኛና የበላይ የሥልጣን አካል በቦርድ መልክ ሊያቋቁም ይችላል።

CCRDA

- በምዕራፍ ሁለት የአዋጁ ክፍል ስለ ማሕበራት የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ይህን የአባላት ማሕበር እና አዲስ አባላትን የማይቀበል ማሕበር የአወቃቀር እና የአሠራር ልዩነት የማያንጸባርቅና በአጠቃላይ በአንደኛው የማህበር ዓይነት ላይ ብቻ ያተኰረ ነው::

- ስለሆነም የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች የሁለቱንም ዓይነት ማህበራት አወቃቀር ከግምት በማስገባት ተስተካክሎና ተሻሽሎ ሊቀረጽ ያስፈልገዋል::

2. የቦርድ ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ

- በምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የመያድ ቦርድ "የሥራ አመራር ቦርድ" (Management Board) ሲሆን በዚሁ መሠረትም ሥልጣንና ተግባሩ ማህበሩን የመምራት፣ የማህበሩን ንብረት የማስተዳደር፣ ማህበሩን የመወከል፣ እና የመሳሰሉ የሥራ አመራር (Management) ሥራዎች ናቸው::

- በአሁኑ ወቅት በመያድ ማሕበረሰብ ውስጥ የሚታወቀውና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው Governing Board ወይም Supervisory Board የሚባለው ነው:: ይህ ቦርድ በዐይነቱና በተግባሩ ከሥራ አመራር ቦርድ (Management Board) የተለየ ሲሆን ዋነኛ የመለያ ጠባዩም የአንድን ድርጅት የሥራ አመራር (Management) ሥልጣንና ተግባር በዋና ሥራ አስኪያጅ ለሚመራው የሥራ አመራር ቡድን (Management team) በመተው የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር አጠቃላይ የሆነ የፖሊሲ አመራር፣ ቁጥጥር፣ እና ድጋፍ ሰጪነት ላይ እያተኰረ መምጣቱ ነው::

- መያድ ድርጅታዊ አቅሙን ከማጐልበት አንጻር ለተቀላጠፈ አሠራር አመቺ የሆነ ድርጅታዊ አወቃቀር ሥራ ላይ በማዋልና የልዩ ልዩ ድርጅታዊ አካሎቹን ሥልጣንና ተግባር ለተቀላጠፈ አሠራር በሚያመች ሁኔታ እያሻሻለ በመምጣቱ፤ በአሁኑ ወቅት በመያድ ማሕበረሰብ ውስጥ ያለው ቦርድ በረቂቅ አዋጁ ከተመለከተው ዓይነት ቦርድ እጅግ የተለየ ነው::

- አሁን በመያድ ማሕበረሰብ ባለው ድርጅታዊ አወቃቀር መሠረት የመያድ የዕለት ተዕለት የሥራ አመራር እና አስተዳደር ሥራ ተጠሪነቱ ለቦርድ በሆነ በዋና ሥራ አስኪያጅ በሚመራ የሥራ አስፈጻሚ ቡድን (management team) የሚፈጸም ነው::

- ስለሆነም የአዋጁ ድንጋጌዎች ይህን በተግባር ያለውንና እያደገም የመጣውን የመያድ ማሕበረሰብ ድርጅታዊ አወቃቀርና የሥልጣንና ተግባር ክፍፍል መሠረት በማድረግ እንደገና ተሻሽሎ ሊቀረጽ ይገባዋል::

CCRDA

3. ስለ ድርጅታዊ አወቃቀር

- የመያድን ቦርድ በሚመለከት ከዚህ በላይ በአጭሩ ከተገለጸው በተጨማሪ የመያድ ድርጅታዊ አወቃቀር እንደ መያዱ ዓይነትና፣ መያዱ እንደሚያስፈጽመው የሥራ አይነት የተለያየና ከአነስተኛ አወቃቀር ጀምሮ ሰፊ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር ድረስ ሊያካትት የሚችል ነው::

- ይኸው ድርጅታዊ መዋቅርም ቋሚ የሆነ ነገር ሳይሆን እንደ ድርጅቱ የሥራ ባሕሪ ማደግ፣ መስፋፋት፣ መቀነስ ወይም መለዋወጥ የተነሳ እና ለሥራ አስፈላጊ ከመሆኑም የተነሳ በየጊዜው ሊለዋወጥ የሚችል ነው::

- በመሆኑም ይህን ተለዋዋጭ የሆነ ድርጅታዊ አወቃቀር ከእነ ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ እንዲሰፍር መጠየቁ በቂ ሕጋዊ ምክንያት የለውም::
- በሕጉ ሊጠየቅ የሚገባው ጉዳይ የአንድ መያድ ከፍተኛውና የበላይ የሥልጣን አካሉን እና ቦርድን በሚመለከት ብቻ አስፈላጊ የሥልጣንና ተግባሩን ዝርዝር በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ማመልከት ነው::

- ከመያዱ ከፍተኛ የሥልጣን አካላት ውጪ የእያንዳንዱ መያድ ውስጣዊ የአስተዳደር መዋቅርና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በመመስረቻ ጽሑፍ የግድ እንዲደነገግ አስፈላጊ አይሆንም::

- በተመሳሳይ ሁኔታም የማህበር ስብሰባ አካሄድን፣ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓትን፣ የውሳኔ ማሳለፍ ሥርዓትን፣ እና የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚመለከት የሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት በማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ ስለመሆኑ እና ሕግ በበቂ ምክንያት አስገዳጅ ድንጋጌ በሚያሰፍርበት ጊዜ ግን በሕጉ የተመለተው ተፈጻሚ መሆኑን ከግምት በማስገባት ድንጋጌዎቹን በዚህ መርሕ መሠረት ማሻሻል ያስፈልጋል::

## IV ምዕራፍ ሶስት ፤ ስለ በጎ አድራጐት ድርጅት (አንቀጽ 66 - 88)

የረቂቅ አዋጁ ምዕራፍ ሶስት ስለ በጎ አድራጐት ድርጅት አመሠራረት፣ ስለ መመስረቻው ጽሑፍ ይዘት ፣ ስለ ምዝገባ፣ ስለ አስተዳደርና የአስተዳደር አካላት፣ ስለ አስተዳደር አካላት አቋቋም ሥልጣንና ተግባር፣ ስለ ስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት እና ስለ ተጠቃሚዎች መብቶች በዝርዝር ይደነግጋል::
ይህን የአዋጁን ክፍል በሚመለከት ከዚህ በታች የተመለከተውን አጠቃላይ አስተያየት እናቀርባለን::

- በረቂቅ አዋጁ የተመለከተው የበጎ አድራጐት ድርጅት አመሰራረት እና አስተዳደር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 483-506 ላይ ከነበሩት ድንጋጌዎች የተለዋወጠ ይዘት አለው::

CGDA

- በእርግጥ ከፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ ሊሻሻሉና ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ድንጋጌዎች የማስተካከሉ ተገቢነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በረቂቅ አዋጁ ላይ አሁን በአለበት መልኩ የተቀመጡት አንዳንድ ድንጋጌዎች ግን በዝርዝር ሁኔታ ላይ ያተኰሩና ለድርጅቱ የውስጥ አሰራር ሊተው የሚገባቸው ሆነው ይታያሉ::

- ለምሳሌም ያህል፣ ስለ ሰብሳቢ አመራረጥ፣ ስለ ስብሰባ አመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ፣ እና የመሳሰሉት በድርጅቱ የውስጥ ደንብ ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው::

- የበጎ አድራጎት ድርጅትን አስተዳደር በሚመለከት ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው የሥራ አመራር ቦርድ እና የበላይ የሥልጣን አካል የሆነው የአስተዳደር ምክር ቤት አደረጃጀት በሚመለከትም ከዚህ በላይ ማህበራትን በሚመለከት ስለ ቦርድ እና ስለ ድርጅታዊ አወቃቀር በሰጠነው አስተያየት መሠረት እንዲታይ ለማስታወስ እንወዳለን::

## V ምዕራፍ አራት ፤ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 89 - 99)

### 1. ገቢ የሚያስገኝ ሥራ

አንቀጽ 90 "ማንኛውም መያድ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መስራት ይችላል" በማለት ይደነግጋል:: መያድ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ገቢ ሊያስገኝ በሚችል ሥራ ላይ ከመሰማራቱም በተጨማሪ አልፎ አልፎ ልዩ ልዩ አይነት የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞች (Fund Raising Programs) በሥራ ላይ እንደሚያውልም ይታወቃል::
ስለዚህም በዚሁ ድንጋጌ ስር ይህ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራም አብሮ ሊጠቀስ የሚገባው ስለሆነ ድንጋጌው በዚህ መንፈስ ተሻሽሎ እንዲጸፍ አስተያየት እናቀርባለን::

### 2. ስለ ታክስ እና ቀረጥ ነጻ መብት

አንቀጽ 91 እና 92 ስለ መያድ የታክስ እና ቀረጥ ነጻ መብቶች ይደነግጋል::
መያድ ነጻ የታክስ መብት ሊሰጠው ከሚገባበት ሥራዎች ውስጥ አንዱ የመያድ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች ናቸው:: መያድ ገቢ በሚያስገኝ ሥራዎቹ የሚገኙ ገቢዎቹ በሙሉ ለመያዱ ዓላማዎች የሚውሉና የመያዱን ትርፍ ማግኘት ያልሆነ ዓላማ የሚያጐለብቱ፣ የሚያስፋፉ እና የሚያዳብሩ ስለሆነ፤ መያድ ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች የሚያገኘው ገቢ ከገቢ ግብር ወይም ታክስ ነጻ ሊሆን የሚገባው ነው::
ስለዚህም የመያድ የታክስና ቀረጥ ነጻ መብት የሚደነግጉት አንቀጾች መያድ የገቢ ማስገኛ ሥራዎቹን በተመለከተም ከገቢ ግብር ወይም ታክስ ነጻ መሆኑን በመግለጽ ተሻሽለው እንዲጸፉ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

CCRDA

## 3. ስለ መያድ ሕብረት (Umbrella Organizations)

አንቀጽ 93 የመያድ ሕብረት (Umbrella Organizations) ለማቋቋም እንደሚቻል ይደነግጋል::
በመያድ ማሕበረሰብ ውስጥ የመያድ ሕብረቶች (Umbrella Organizations) ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ዓይነት እና ደረጃ ያላቸው የሕብረት ሕብረቶች (Network of Networks) ጭምር ይገኛሉ:: እንዲህ ያለው የቅንጅት አሠራር በየሥራ ዘርፉ (sectoral) እና ሁሉንም አይነት የሥራ ዘርፎች በሚያካትት መልኩም (cross-sectoral) ይገኛል:: ስለዚህም ይህ ስለ መያድ ሕብረት ማቋቋም የሚደነግገው አንቀጽ ከዚህ በላይ የተገለጸውን በመያድ ማሕበረሰብ ያለውን የቅንጅት እድገት (Development of Networks) በተሟላ መልኩ የሚያካትት እንዲሆን አንቀጹ በዚህ መንፈስ ተሻሽሎ እንዲጸፍ አስተያየት እናቀርባለን::

## 4. ስለ ይግባኝ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 94 መዝጋቢው ጽ/ቤት ምዝገባን እገዳን እና ሥረዛን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው ጽ/ቤት የበላይ አካል ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል:: (በአንቀጽ 94 ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ ሊቀርብባቸው ስለሚችሉት ሁኔታዎች የተጠቀሱት አንቀጾች የሕትመት ስህተት ያለበት ስለሚመስል በዚህ አንቀጽ ስር ለመጠቀስ የተፈለጉት አንቀጾች 19፣ 20፣ 22፣ 30 እና 33 /2/ እንደሆኑ ግምት እንወስዳለን::)

በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተፈቀደው የይግባኝ ዓይነት አስተዳደራዊ ይግባኝ (Administrative review/appeal) ብቻ ሲሆን፣ በአስተዳደራዊ ውሳኔው ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ የተደነገገ ነገር የለም::

ለመዝጋቢው ጽ/ቤት የበላይ አካል የሚቀርበውን ይግባኝ በተመለከተም በአጠቃላይ አነጋገር ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል መሆኑ ከመገለጹ በስተቀር ይግባኙ ቀርቦ ስለሚታይበትና ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሥርዓት የተደነገገ ነገር የለም::

ስለሆነም ይግባኝን የሚመለከተው ድንጋጌ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መርሆዎችና ነጥቦች መሠረት በማድረግ ተሻሽሎ እንዲጸፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

- መያድ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ እንደማይገባው ያቀረብነው መሠረታዊ መርሕ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤት እገዳን፣ ስረዛን፣ ምዝገባን ጨምሮ በሌሎች በማናቸውም ጉዳዮች ላይ በሚወስደው ውሳኔ በቅድሚያ አስተዳደራዊ ይግባኝ (Administrative review/ appeal) እና አስተዳደራዊ ውሳኔው በወቅቱ ካልተገኘ ወይም ባለጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሳኔው የማይስማማ ቢሆን በሁለተኛ ደረጃ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ይግባኝ (Judicial appeal) የሚቻል መሆኑ በግልጽ ሊደነገግ ይገባል::

- ማናቸውም ባለጉዳይ በይግባኝ አቤቱታው ላይ በቂ ዝግጅት አድርጎ ይግባኙን ለማቅረብ ያስችለው ዘንድ ለይግባኝ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ 30 ቀን ሳይሆን እንደ ማናቸውም የፍትሐብሔር ጉዳዮች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተደነገገውን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ በመከተል 60 ቀን ሊሆን ይገባዋል::

CCRDA

- አስተዳደራዊ ይግባኝን በሚመለከት ማንኛውም ባለጉዳይ የምዝገባ ጽ/ቤቱ ውሳኔ በጽሑፍ በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ለፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል::

- የምዝገባ ጽ/ቤቱ ውሳኔ በጽሑፍ ያልተሰጠ ከሆነ በማናቸውም ጊዜ ይግባኙን ለማቅረብ ይቻላል::

- ማንኛውም ይግባኝ የሚቀርበው በጽሑፍ ሆኖ የይግባኙን ምክንያት በግልጽ የሚዘረዝር መሆን አለበት:: የይግባኝ አቤቱታ ከመያድ የቦርድ አባሎች ውስጥ በአንዱ፣ በመያዱ የሥራ መሪዎች፣ ከመያዱ አባሎች በአንዱ ወይም የመያድ ምዝገባ ጥያቄ ካቀረቡ ባለጉዳዮች በአንዱ ወይም ጉዳዩ በሚያገባው ሰው ተፈርሞ ሊቀርብ ይችላል::

- ሚኒስትሩ የቀረበለትን ይግባኝ ባለጉዳዮቹን አስቀርቦ ከአዳመጠና ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የምዝገባ ጽ/ቤቱን ውሳኔ ሊሽረው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀድቀው ይችላል:: በማናቸውም ጊዜ ሚኒስትሩ በቀረበለት ይግባኝ ላይ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት::

- በማናቸውም ጉዳይ ላይ ሚኒስትሩ በቀረበለት ጉዳይ ላይ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል ውሳኔውም በሚኒስትሩ ተፈርሞበት ለይግባኝ ባዩ ይሰጠዋል:: ይኸውም ውሳኔ:-

    - በይግባኝ የታየውን ነገር ሁኔታ ይዘረዝራል

    - የቀረቡትንና የተመረመሩትን ለጉዳዩ ተገቢ የሆኑትን ምስክርነትና ማስረጃዎች ሚዛናቸውንና የተገኙበትን ሥፍራ ይገልጻል፣

    - ሚኒስትሩ ያገኛቸውን ርትዕ የሆኑ ነገሮች ይገልጻል:: ደግሞም ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው እርስበርሳቸው በግልጽ የሚቃወሙ ማስረጃዎች የተገኙ እንደሆነ የእነዚህን ሚዛንና በምን ምክንያት ተፈልሶውን እንደ አብራራውና ውሳኔውን እንዲሰጥ በምን መንገድ እንደመሩት ይገልጻል፣

    - የቀረበለትን ክርክር ውሳኔ ያሠፍራል

    - ውሳኔው የሚፈጸምበትን አፈጻጸም ይገልጻል::

(ከዚህ በላይ የቀረበው የይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት የተወሰደው እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ ካለው የማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 325/1959 አንቀጽ 16 ላይ ነው::)

- ከዚህ በላይ ዝርዝሩ የቀረበው አስተዳደራዊ ይግባኝን በሚመለከት ሲሆን፣ የተባለው አስተዳደራዊ ውሳኔ በሚኒስትሩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተሰጠ ወይም ይግባኝ ባዩ በሚኒስትሩ ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ በግልጽ ሊደነገግ ይገባል::
(ከጉዳዩ ፀባይ የተነሳ እንደዚህ ያለው ይግባኝ ሊቀርብ የሚገባው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን:)

CCRDA

- በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (Justiciable matter) ለፍርድ ቤት የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37 ስር የተደነገገ መሠረታዊ የሆነ ፍትሕ የማግኘት መብት ስለሆነ፤ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት በግልጽ ሊደነገግ ይገባዋል::

## 5. ስለ መሸጋገሪያ ድንጋጌ

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 95 እስከ አሁን ድረስ ባለው ሕግ ተመዝግበው በሥራ ላይ ያሉ ድርጅቶች ሁሉ አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ወደ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽግግር ምዝገባ እንዲፈጽሙ ይደነግጋል::

ይህ ሁኔታ ለአሠራር እጅግ አስቸጋሪና በመዝጋቢው ጽ/ቤት ላይም እጅግ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር ስለሆነ፤ እስከ አሁን ድረስ በነበረው ደንብ እና አሠራር ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ የነበሩ ድርጅቶች ሁሉ በአዲሱ ሕግ መሠረት እንደተመዘገቡ ይቆጠራል በሚል ተሻሽሎ እንዲጻፍ አስተያየታችንን እናቀርባለን::

CCRDA

## ሁለተኛ ክፍል

## የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት መቋቋምን በሚመለከት

የመያድን ተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ (Operational activity) በተመለከተ የመያድ ማሕበረሰብ አንድ እራሱን የቻለ የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት (Office of Voluntary Organizations) እንዲቋቋም ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል::

የመያድ ማሕበረሰብ አሁን በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ እንደተመለከተው የመያድ ምዝገባ ጽ/ቤት (NGO Registration Office) እራሱን የቻለ አንድ ሕጋዊ አካል ሆኖ መቋቋሙን በአድናቆት እየተቀበለ፤ በዚሁ አጋጣሚ ግን ስለ የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት መቋቋም ሲያቀርብ የነበረውን ጥሪ በድጋሚ ለማስታወስ እና የዚህ ጽ/ቤት በአስቸኳይ መቋቋምን አስፈላጊነትም አጠንክሮ ለማሳሰብ ይፈልጋል::

የመያድ ምዝገባን በሚመለከት እራሱን የቻለ ጽ/ቤት መቋቋሙ ለመያድ አመሠራረት እና አሠራር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው እርምጃ እንደሆነ እየተረዳን፤ ከዚህ ምንም ባልተናነሰ መልኩ ትኩረት የሚሻው የመያድ ከተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች (Operational activities) ጋር በተያያዘ ያለው ባለ ብዙ ፈርጅ ችግር አስቸኳይ እና ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው መሆኑ ነው::

በዚህ ረገድ በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ በመያድ ማሕበረሰብ በቀረበው ጥያቄ መሠረት የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት መቋቋም ነው:: ይህ ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት በየመሥሪያ ቤቱ ባልተቀናጀ መልኩ ተበታትኖ ያለውን አሠራር በማሰባሰብ ለመያድ ሥራዎችና ጉዳዮች እራሱን የቻለ ዋነኛ መንግሥታዊ አካል (one focal governmental agency) በመሆን የሚያገለግል ጽ/ቤት ነው::

መያድ በአገሪቷ የልማት ዕድገት ጥረት ውስጥ ያለውና ሊኖረው የሚችለው ተሳትፎ እጅግ ከፍተኛና ገና ሙሉ በሙሉ በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ስለሆነ፤ ይህን በበጎ ፈቃደኝነት ዘርፍ ያለውን የሰው፣ የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የበጎ ፈቃደኝነት ሀብት በአግባቡ ለመጠቀምና በልማት ሥራ ላይ ለማዋል ያስችል ዘንድ ለዚህ ጉዳይ አንድ እራሱን የቻለ መንግሥታዊ አካል መቋቋሙ የግድ አስፈላጊ ነው::

በበጎ ፈቃደኝነት ዘርፍ ያሉት የልማትና የእድገት ተዋናዮች ሥራቸውን የሚያመቻችላቸው፣ ቅንጅት የሚፈጥርላቸው እና አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ የሚሰጣቸው አንድ ዋነኛ ሥራው ይኸው ብቻ የሆነ መንግሥታዊ አካል ያስፈልጋል:: ይህ አካልም የመያድን ሥራ ለመከታተል፣ እና ለመገምገም (Monitoring and Evaluation) ሥልጣን የሚኖረው ይሆናል::

የበጎ ፈቃደኝነት ድርጅቶች ጽ/ቤት በአጠቃላይ ከመያድ ምዝገባ ውጪ ላሉ የመያድ ጉዳዮች ሁሉ አንድ እራሱን የቻለ አካል ሆኖ የሚሰራ ሲሆን በመያድ እድገት እና መስፋፋት፣ በመያድ ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፣ እንዲሁም በመያድ ሥራዎች ክትትል፣ ግምገማ እና መረጃ ረገድ ዋነኛ ኃላፊነት የሚኖረው ጽ/ቤት ይሆናል::

CCRDA

ይህ ጽ/ቤት በበቂ የሰው ሃይልና አስፈላጊ የማቴሪያልና የገንዘብ አቅም ሊመሰረት የሚገባው ሲሆን አወቃቀሩን በተመለከተም በቀጥታ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ስር ወይም እንደተገቢነቱ መጠን የመያድ ሥራ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች በአንደኛው ስር ሊደራጅ የሚችል ነው::

ከዚህም አንጻር አሁን የአለውን የፌዴራል አወቃቀር ደረጃ ተከትሎ በክልሎችም ጭምር የተደራጀ አወቃቀር ያለውን አግባብ ያለው መንግሥታዊ መ/ቤት ለዚህ አገልግሎት ለማዋል የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አለ::

የዚህ ጽ/ቤት የበላይ አካል ቦርድ እንዲሆንና የቦርዱም አንድ ሶስተኛ አባላት ከተለያዩ ዓይነት መያዶች የሚወከሉ አባላት የሚሳተፉበት እንዲሆንም ጭምር አስተያየታችንን እናቀርባለን::

CCRDA

# አባሪዎች

አባሪ "ሀ" : መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅ

አባሪ "ለ" : የመያድ ማሕበረሰብ የሕግ ጉዳዮች ምክክር ግብረ ሐይል በመያድ ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅ ላይ ያቀረበው የቅድሚያ አስተያየት

አባሪ "ሐ" : የመያድ ምዝገባና አሠራር ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየው ዓውደ ጥናት ተሳታፊ የነበሩ ድርጅቶች ዝርዝር

CCRDA